# የኢንዱስትሪ ዘርፍ
# የሙስና መከላከል እና ሥነ-ምግባር ግንባታ

## (ማሰልጠኛ ሞጁል)

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን
FEDERAL ETHICS & ANTI-CORRUPTION COMMISSION

**— ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ —**

**CORRUPTION FREE ETHIOPIA**

ህዳር 2017 ዓ.ም
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

# የኢንዱስትሪ ዘርፍ የሙስና መከላከል እና ሥነ-ምግባር ግንባታ

# (የሥልጠና ሞጁል)

ህዳር 2017 ዓ.ም

አዲስ አበባ

ኢትዮጵያ

# የኢንዱስትሪ ዘርፍ የሙስና መከላከል እና ሥነ-ምግባር ግንባታ

# (የሥልጠና ሞጁል)


አዘጋጆች፡

ዘውዴ ዛኬ ኮይራ (ፒ.ኤች.ዲ)-ከኢት/ያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ

ፍቃዱ በልዳ ከበደ (ረዳት ፕሮፌሰር) -ሐረማያ ዩኒቨርሲቲ

አርታኢ፡-

አቶ ሀረጎት አብርሃ

አቶ የኋላሸት ደሳለኝ

አቶ ቤዛ በኃይሉ

አቶ አንተነህ ሀይሌ

ግራፊክስ ዲዛይን፡-

አቶ በለጠ ብርሀኑ



© የፌደራል የሥነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን



ህዳር 2017 ዓ.ም

## ማዉጫ

ይዘት ገጽ

ማዉጫ ........ II

የሞጁሉ አጠቃላይ መግለጫ ........ V

መግቢያ ........ V

ተተኳሪ ሰልጣኞች ........ VIII

የሞጁሉ አስፈላጊነት ........ IX

የግምገማ ዘዴዎች ........ IX

የማሰልጠኛ ዘዴዎች ........ X

ለስልጠናዉ የሚያስፈልጉ ግበዓቶች ........ X

የሞጁሉ ዓላማዎች ........ X

ምዕራፍ አንድ ........ 1

የሙስና ወንጀል ምንነት ........ 1

1.1. መግቢያ ........ 1

1.2. የምዕራፉ ዓላማ ........ 1

1.3. የተፈቀደው ሰዓት ........ 1

1.4. የማነቃቂያ ጥያቄዎች ........ 1

1.5. የሙስና ወንጀል ምንነት ........ 2

1.6. የሙስና ዓይነቶች ........ 3

1.6.1. ዝቅተኛ ሙስና (petty corruption) ........ 4

1.6.2. ከፍተኛ ሙስና (Grand corruption) ........ 4

1.6.3. ስርዓታዊ ሙስና (systemic capture) ........ 5

1.6.4. ፖለቲካዊ ሙስና (political Corruption) ..... 5
**1.7. የሙስና ወንጀል ልዩ ባህርያት ..... 6**
1.7.1. የወንጀሉ አፈጻፀም ስልት ..... 7
1.7.2. የሙስና ወንጀል የሚስከትለዉ ጉዳት ..... 7
1.7.3. የወንጀል ፈጻሚዎች አቅም ..... 7
1.7.4. በወንጀሉ ቀጥተኛ ተጎጂ ግለሰብ አለመኖር ..... 8
1.7.5. ድንበር ተሻጋሪነቱ ..... 8
**1.8. በአዋጅ ቁጥር 881/2007 የተደነገጉ የሙስና ወንጀሎች ..... 9**
**ምዕራፍ ሁለት ..... 21**
**የኢንዱስትሪ ዘርፍ ለሙስና ያለው ተጋላጭነትና ዘርፉን የሚመለከቱ ብልሹ አሰራሮች ..... 21**
**2.1. መግቢያ ..... 21**
**2.2. የምዕራፉ ዓላማ ..... 21**
**2.3. የተመደበው ጊዜ ..... 22**
**2.4. የማነቃቂያ ጥያቄዎች ..... 22**
**2.5. የዘርፉ ለሙስና ተጋላጭነት ..... 22**
**2.6. በዘርፍ የሚስተዋሉ ሙስና እና ብልሹ አሰራሮች ..... 28**
**2.7. የማጠቃለያ ጥያቄዎች ..... 31**
**2.8. ማጠቃለያ ..... 32**
**ምዕራፍ ሶስት ..... 34**
**በኢንዱስሪ ዘርፍ የሚስተዋለው ሙስና የሚያስከትለዉ ጉዳትና የመከላከያ ስልቶች ..... 34**
**3.1. መግቢያ ..... 34**
**3.2. የምዕራፉ ዓላማ ..... 35**
**3.3. የተመደበው ጊዜ ..... 35**

3.4. የማነቃቂያ ጥያቄዎች ........ 35
3.5. ሙስናና ብልሹ አሰራሮች የሚያስከትሉት ጉዳቶች ........ 38
3.5.1. በተቋም ደህንነት ላይ ........ 38
3.5.2. በማህበረሰብ ደህንነት ላይ ........ 39
3.5.3. በአከባቢ ደህንነት ላይ ........ 39
3.5.4. በኢኮኖሚ ላይ ........ 43
3.6. የኢንዱስትሪ ዘርፍ የሙስና መከላከያ ስልቶች ........ 46
3.7. በኢንዱስትሪ ዘርፍ የሙስና ስጋቶች መከላከያ ስልቶች ........ 52
3.8. የማጠቃለያ ጥያቄዎች ........ 54
3.9. ማጠቃለያ ........ 55
4. ዋቢ ........ 57
አባሪ አንድ፡ ራስን መገምገሚያ ቼክ ሊስት ........ 58
አባሪ ሁለት፡ በሰፊ ቡድን ለማወያያ የሚሆኑ ጥያቄዎች ........ 62

# የሞጁሉ አጠቃላይ መግለጫ

## መግቢያ

ይህ ሞጁል ሰልጣኞች በፀረ-ሙስና ዙሪያ በሚያደረጉት ውይይቶች ብልሹ አሰራሮችን፤ የሙስና ምንጮችን፣ መገለጫዎችን፤ መከላከያ ስልቶችን፣ የሚያስከትሉትን ጉዳቶች ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር እና ተጠሪ ተቋማት አሠራር አንፃር እንዲቃኙት ተስቦ ይተዘጋጀ ነዉ።

ለበርካታ አስርት ዓመታት ሙስና እንደ ትልቅ ዓለም አቀፋዊ ችግር እና ለድህነት፣ ለደህንነት መታጣት ለኢፊትሐዊነት፤ እና ለግጭት ዋነኛ መንስኤ እየሆነ መጥቷል። በተለይ ባለፉት አስርት ዓመታት ጉዳዩ የአገር መሪዎች፤ የዓለም አቀፍ የገንዘብና የፖሊሲ ተቋማት፣ ኮርፖሬሽኖች፣ አክቲቪስቶች እና የመገናኛ ብዙሃን ትኩረት ስቧል። በአገራችን ኢትዮጵያ ውስጥ ደግሞ የመንግስት ሃላፊዎችና ሰራተኞች በሙስና ላይ የሚሳተፉ መሆናቸውን በመንግስት ከፍተኛ ሃላፊዎች ደረጃ ከሚነሳዉ ሃሳብ መረዳት ይቻላል። የመንግስት ባለስልጣናትና ሰራተኞች መንግስት ለሙስና የዘረጋዉን ቀይ መስመር እንደ ቀይ ምንጣፍ እየተጠቀሙበት ይገኛሉ። ሌብነት እንደ መብት እየተቆጠረ ነው። የመሬት ወረራ ለመንግስት ባለስልጣናትና ሰራተኞች የሀብት ማመንጫ ዋና ዘዴ ሆኗል፣ ከመደበኛ ደላሎች በተጨማሪ ህብረተሰቡን ማገልገል የሚገባቸው የመንግስት ሰራተኞች የተጣለባቸውን ህዝባዊና አገራዊ አደራ ወደ ጎን በማለት ሙስናን እንደ ሀብት ማካበቻ ቀላል ዘዴ በመቁጠር በስፋት እየተሳተፉበት ይገኛሉ በማለት ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናት ይገልጻሉ (ADDIS STANDARD, 2022)።

በመሆኑም የፌደራል የሥነምግባርና የፀረሙስና ኮሚሽንም በመንግስት የተጣለበትን ተልዕኮ ማሳካት የሚያስችሉ ዘርፍ ተኮር የሙስና መከላከል ስልቶችን በመንደፍ እየሰራ ይገኛል። በየዘርፉ የሚዘጋጁት ሞጁሎችም የተልዕኮዉ አንዱና ዋነኛዉ አካል ናቸው።

መንግስትም የኢንዱስትሪ ዘርፍ ለአገር ያለውን ፋይዳ በመገንዘብ የኢፌድሪ ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በአዋጅ ቁጥር 1263/2014፣ የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት በደንብ ቁጥር 526/2014 እና የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት በደንብ ቁጥር 504/2014 አቋቁሟቸዋል።

የኢንዱስትሪ ዘርፍ የአገሪቱ የኢኮኖሚ የጀርባ አጥንት በመሆኑ ትኩረት ከተሰጣቸው ተቋማት አንዱ ነው። የኢንዱስትሪ ዘርፍ "በ2022 የአምራች ዘርፍ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ሆኖ ማየት" የሚል ራዕይ አንግቦ በመስራት ላይ ይገኛል። አሁን ባለንበት ወቅት የኢንዱስትሪ ዘርፍ ኢንቨስትመንትን በማስፋፋት፣ የውጭ ምንዛሪ ግኝትን በማሳደግ፣ ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታቸው ጉልህ የሆኑ ገቢ ምርቶችን በመተካት፣ ለዜጎች የሥራ ዕድልን በመፍጠር፣ የዘርፍ ማህበራትን ማጠናከር፣ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ፣ የጥናትና ምርምር እንዲሁም የማማከር ስራዎችን በማሳደግ፣ የአነስተኛና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎችን ሽግግር በማሳለጥ እና የዘርፉን ተልዕኮ ለማሳካት ዘርፈ ብዙ ስራዎች ከማከናወናቸው ጋር ተያይዞ በኢትዮጰያ ታምርት የተጀመረውን ንቅናቄ ለማሳካት የሚከተሉትን ስትራቴጅዎች ከግብ ለማድረስ እየተጋ ይገኛል።

የፌዴራል የስነምግባርና የጸረ ሙስና ኮሚሽኝን በ2015 ዓ/ም የኢንዱስትሪ ዘርፍ የሙስና ሥጋት ግምገማዊ ጥናት በሚል ርዕስ ከተዘጋጀዉ ሞጁል የተወሰደዉ መረጃ እንድሚያሳይዉ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌደራል መንግሥት አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ 1263/2014 መሰረት የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል። እነዚህም ሥልጣናትና ተግባራት የኢንዱስትሪ ዘርፍ ለሙስና ያለው ተጋላጭነትን፣ በኢንዱስትሪ ዘርፍ የሚስተዋሉ ሙስና እና ብልሹ አሰራሮችን፤ በኢንዱስትሪ ዘርፍ የሚስተዋሉ ሙስና እና ብልሹ አሰራሮች የሚያስከትሉት ጉዳቶችንና በኢንዱስትሪ ዘርፍ የሚፈፀሙ የሙስና ተግባራት መከላከያ ስልቶችን ለመለየት፣ ለመገምገም፤ ለመለየት፤ ትንተና ለመስጠትና፤ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልተናዎችን ለመስጥት የመሰረት ድንጋይ ናቸዉ። እነሱም የሚከተሉት ናቸዉ፦

- የኢንዱስትሪ በተለይም የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማትንና ተወዳዳሪነትን በቀጣይነት የሚያረጋግጡ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን፣ ፕሮግራሞችን እና ሕጎችን ያመነጫል፣ ለአፈጻጸሙ ከሀገራዊ የልማት አቅጣጫ ጋር የተጣጣመ ዝርዝር መርሀ-ግብር ያዘጋጃል፤ በሚመለከተው አካል ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤
- በኢንዱስትሪ በተለይም በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ የግል ዘርፉን ተሳትፎና ሚና ለማሳደግ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ ለአፈጻጸሙ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፤

- በኢንዱስትሪ በተለይም ማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ልማት ትኩረት የሚሠጣቸውን ጨርቃ ጨርቅ፣ ቆዳ እና የምግብና መጠጥ ኢንዱስትሪዎችና የመሳሰሉት ንዑስ ዘርፎች ካላቸው አንጻራዊ ጠቀሜታና እምቅ አቅም አኳያ ይለያል፤ ለአፈጻጸሙ ዝርዝር ከሀገራዊ የልማት አቅጣጫ ጋር የተጣጣመ መርሀ-ግብር ያዘጋጃል፤ በሚመለከተው አካል ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

- በዘርፉ ምርምርና ጥናት የሚያካሂዱ አካላትን አስፈላጊውን ድጋፍ በማድረግ የኢንዱስትሪዎችን፣ የኢንቨስትመንት እና የማኑፋክቸሪንግ አቅምና ተወዳዳሪነትን እንዲያድግ ያደርጋል፤ በኢንቨስትመንት ሕግ መሠረት የሀገር ውስጥ እና የውጭ ባለሃብቶች በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ኢንቨስትመንት የሚሳተፉበትን ሁኔታዎች ያመቻቻል፤ በሥሩ ያሉ ተጠሪ ተቋማት በዋናነት ለሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ድጋፍ እንዲሰጡ ለማድረግ ተገቢውን ሥርዓት ይዘረጋል፣ ያስፈጽማል፤

- የኢንዱስትሪ በተለይም የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ልማትን ለማሳደግ የሚያስችሉ ተግባራትን፤ የምርጥ ተሞክሮ መቀመር፣ እና አጠቃላይ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት አቅም ግንባታ ሥራዎችን ይሰራል፤

- የኢንዱስትሪ በተለይም የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ልማትና ምርታማነትን ለማሳደግ ኢንዱስትሪዎች የኤክስቴሽን አገልግሎት፣ የቴክኖሎጂ፣ የግብዓትና የግብይት እንዲሁም በአመራረት ረገድ ድጋፍ እንዲያገኙ ያደርጋል፤ ውጤታማነታቸውንም ያረጋግጣል፤

- የኢንዱስትሪ በተለይም የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ምርቶች የጥራት ደረጃቸውን የጠበቁ፣ በዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የአቅም ግንባታ፣ የምርምርና ስርጸት ሥራዎች እንዲከናወኑ ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

- ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ለኢንዱስትሪ በተለይም ለማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ አስፈላጊ የሆነው የሰው ኃይል ፍላጎት እና አስተማማኝ ግብዓት ለማሟላት የሚቻልበትን ስልት ይቀይሳል፤ ከሚመለከተው ዘርፍና አካላት ጋር

- በመሥራት የኢንዱስትሪ ግብዓት አቅርቦት ትስስር ሥርዓት እንዲዘረጋ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤ ተግባራዊ ያደርጋል፤

- ለዘርፉ እድገት ከሚመለከታቸው የፌደራልና የክልል አካላት ጋር በቅንጅት ይሠራል፣ ለዘርፉ አሳታፊና ዘላቂ መዋቅራዊ ለውጥ ስለሚመጣበት ሁኔታ ስልቶችን ይነድፋል፣ ተግባራዊ የሚሆኑበትን ሥርዓት ይዘረጋል፤
- ለማዕድን ሚኒስቴር ከተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት ውጪ ያሉ ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታቸው ጉልህ የሆኑ የኢንዱስትሪ ገቢ ምርቶች በሀገር ውስጥ ምርቶች እንዲተኩ ድጋፍ ያደርጋል፤
- በአነስተኛ፣ በመካከለኛና በከፍተኛ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች መካከል የተቀናጀ ትስስር እንዲፈጠርና ስኬታማ ሽግግሮች እንዲከናወኑ የሚያስችሉ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች እና የአሠራር ሥርዓቶችን ይዘረጋል፤
- የአነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞችን ውጤታማ እንዲሆኑ የማትጊያ ስልት ይቀይሳል፣ ድጋፍ ያደርጋል፤
- የኢንዱስትሪ በተለይም የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች በአካባቢ ጥበቃ የተቀመጡ መስፈርቶችን እንዲያሟሉ ድጋፍ ያደርጋል፤
- የኢንዱስትሪ፣ የዘርፉ እና የሙያ ማህበራት እንዲቋቋሙ ያበረታተል፣ የተቋቋሙትንም እንዲበረታቱ ያደርጋል፡፡

## ተተኳሪ ሰልጣኞች

ይህ የስልጠና ሞጁል ትኩረት የሚያደርገዉ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፤ የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት እና የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት አመራሮችና ሰራተኞች ናቸው፡፡ የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ዘርፍ የሚያካትታቸው ንዑሳን ዘርፎች፤ -ጨርቃ ጨርቅና አልባሳት፣ የምግብና መጠጥ፣ የቆዳና ቆዳ ውጤቶች፣ የኬሚካልና የኮንስትራክሽን ግንባታ ግብአቶችን፣ እና የብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ቴክኖሎጂ ናቸው፡፡ የኢንተርፕርይዝ ልማት ዘርፍ የሚያካትታቸው ጥቃቅን፤አነስተኛ እና መካከለኛ ማኑፋክተርንግ ኢንተርፕራይዞችን ነው፡፡ በተጨማሪም የኢትየጵያ ካይዘን ኢንስቲትዩትንም ያካትታል፡፡

## የሞጁሉ አስፈላጊነት

የፌዴራል የሥነ ምግባር እና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ባደረገው የዳሰሳ ጥናት በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ እየታየ ያለው ሙስናና ብልሹ አሠራር የፖለቲካ፣ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግር ከመሆኑም ባሻገር አገሪቱን ለከፋ ቀውስ እየዳረጋት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

እንደማሳያ ማህበረሰቡ በመንግሰት ተቋማት አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ቅሬታ እያሰማ መሆኑ፣ ዜጎች በመንግስት ተቋማት አመኔታቸው እየቀነሰ መምጣቱ፣ የአገልግሎት አሰጣጥ መጓተት፣ ተደጋጋሚ ኦዲት ግኝቶ መበራከትና የመሻሻያ ሀሳቦችን አለመተግበር፣ የገበያ ስርዓቱ የተረጋጋ አለመሆንና በቴክኖሎጂ የተደገፈ የግዥ ዘዴን አለመጠቀም፣ የተጠያቂነት ማነስ ጥቂት ማሳያዎች ናቸው፡፡ በመንግስት ተቋማት ለሚታዩት የሙስና እና ብልሹ አሰራሮችን ለመከላከል የሚያስችል የቁጥጥር ስርዓት ማነስ፣ የህግ የበላይነት ድክመት፣ ጠንካራ ቅንጅታዊ አሰራር አለመኖር ፣ የግልፅነትና ተጠያቂነት ክፍተቶች መበራከት እንደመንስኤ የሚነሱ ናቸው፡፡

የጥናቱ ውጤት እንደሚያሳየው ይህንን ችግር ለመፍታት ከሚቻልባቸው መንገዶች አንዱ በተለያዩ የመንግስት እርከኖች ሰፊ ስልጠና በመስጠት ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ሞጁል በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣ በኢትየጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት እና በአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ውስጥ ለሙስና የሚያጋልጡ ብልሹ አሰራሮችን ለመቅረፍ በሚደረግዉ ሂደት ስልጠና ለመስጠት የተዘጋጀ ነው፡፡

## የግምገማ ዘዴዎች

በስልጠና ሞጁሉ በተካተቱት ፍሬ ሃሳቦች ዙሪያ የሰልጣኞችን ቅድመ እና ድህረ ግንዛቤና ዕውቀት መገምገም ተገቢ ነው፡፡ በመሆኑም አሰልጣኞች ስልጠና ከመጀመሩ በፊት እንዲሁም ስልጠናው ከተጠናቀቀ በኋሊ በዚህ ሞጁል መጨረሻ አባሪ አንድ ስር የተቀመጠዉን ሞዴል በማስሞላት፤ የስልጠናው ግብ መሳካቱን መረዳት እና በቀጣይ የሚሰጡ ስልጠናዎች ግብዓት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ራስን የመገምገሚያ ቼክ ሊስቱ በዚህ ሞጁል መጨረሻ አባሪ አንድ ስር ይገኛል፡፡

## የማስልጠኛ ዘዴዎች

በስልጠና ወቅት አሰልጣኞች የሚከተሉትን የማስተማሪያ ዘዴዎች ስራ ላይ እንዲያዉሉ ይመከራል:: እነሱም፦

- የአእምሮ ጎዳ ማንኳኳት (Brainstorming)
- ገለጻ
- አስረጅ ናሙና (Case studies)
- የቡድን ውይይት
- የጥንድ ዉይይት
- ጥያቄ እና መልስ
- በግል ጥያቄዎችን መስራት

## ለስልጠናዉ የሚያስፈልጉ ግበዓቶች

በአጠቃላይ ለዚህ ስልጠና የሚያስፈልጉ ግባዓቶች፦

- LCD ፕሮጀክተር
- ፓወር ፖይንት
- ኮምፒዩተር
- የስልጠናው ሞጁል
- ፍሊፕ ቻርት
- ማርከር
- የማስታወሻ ደብተሮች
- የጽህፈት መሳሪያዎች
- ለቡድን ሥራ ምቹ የሆነ ቦታ

## የሞጁሉ ዓላማዎች

ይህ የሥልጠና ሞጁል በግለሰብ እና በተቋማት ደረጃ ጠቃሚ የሆኑ ዋና እና ንዑሳን ዓላማዎች አሉት::

## ዋና ዓላማ

የዚህ የሥልጠና ሞጁል ዋና ዓላማ በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣ በኢትየጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት እና በአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ለሙስና እና ብልሹ አሰራር ተጋላጭ የስራ ዘርፎችንና የአሰራርር ስርዓቶችን መጠቆም፣ የማሻሻያ ምክረ ሃሳቦችን በማመንጨት፣ የሙስና መከላከል ስልትን ማመላከት እና ሙስና እና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል የሚደረገዉ ጥረትን በማገዝ ወደ ላቀ ደረጃ ማድረስ ነዉ፡፡

## የሞጁሉ ንዑሳን ዓላማዎች

የኢንዱስትሪ ሚኒስቴርና ተጠሪ ትቋማት ሰልጣኝ ሰራተኞች ከስልጠና ብኋላ፡-

- የሙስና ጽንሰ-ሀሳቦችን ያብራሩሉ፤
- በኢንዱስትሪና ተጠሪ ትቋማት ዘርፍ ያሉትን የሙስና ወንጀል ዓይነት ይለያሉ፤
- በተቋማቸዉ የሚስተዋሉትን ለሙስና የሚያጋልጡ ብልሹ አሰራሮችን ነቅሰዉ ያወጣሉ፤
- ሙስናን ለመከላከል በዘረፉ ዉስጥ ያሉ ሰራተኞችን ሚና ያብራሩሉ፤
- ሙስናን ለመከላከል በስልጠናዉ የተገኙ መልካም ተሞክሮዎችን ይተገብራሉ፣
- በዘርፉ የሚስተዋለዉ የሙስናና ብልሹ አሠራር በአገሪቱ ሁለንተናዊ እድገት፣ በሕብረተሰብ፣ በአካባቢና በዘርፉ ላይ የሚኖረውን አሉታው ተፅዕኖን ያስረዳሉ፤
- በዘርፉ የሚስተዋሉትን የሙስናና ብልሹ አሠራሮችን ለመከላከል በሚደረገው አገራዊ ንቅናቄ ላይ በንቃት ይሣተፋሉ፤

**ለሞጁሉ ሥልጠና የተመደበው አጠቃላይ ጊዜ:-** 12:00 ሰዓት (አንድ ከግማሽ ቀን)

## ምዕራፍ አንድ

## የሙስና ወንጀል ምንነት

### 1.1. መግቢያ

የሙስና መከላከል ስራን በተጨባጭ ለመስራት ስለሙስና ወንጀል ምንነት አስቀድሞ መረዳት ተገቢ ነው፤ ምክንያቱም ብዙ ሰዎች የሙስና ወንጀልን ከጉቦ መስጠትና መቀበል ጋር ብቻ አያይዘው ስለሚረዱት ነው፡፡ ይሁንና ለሙስና ምንነት አንድ አለም አቀፋዊ ብያኔ መስጠት ባይቻልም የሙስና ወንጀል መገለጫዎችን ግን ዘርዝሮ ማየት ይቻላል፡፡ በመሆኑም ሰልጣኞች በሙስና መከላከል ዙሪያ ተገቢውን እውቀትና ክህሎት እንዲያገኙ ይህ ምእራፍ የሙስና ወንጀል ምንነትና መገለጫዎችን የሚቀርቡበት ምእራፍ ነው፡፡

### 1.2. የምዕራፉ ዓላማ

ከዚህ ምእራፍ ስልጠና በኋላ ሰልጣኞች፡-

1. የሙስና ወንጀል ምንነትን ይለያሉ፤
2. በሀገራችን ያሉትን የሙስና ወንጀሎች መገለጫዎችን ይዘረዝራሉ፤

### 1.3. የተፈቀደው ሰዓት

ይህን ምእራፍ ለማጠናቀቅ የተመደበው ጊዜ 1፡30 ሰዓት

### 1.4. የማነቃቂያ ጥያቄዎች

<u>ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች አንብቡና ከጎናችሁ ካለው ተሳታፊ ጋር ተወያይታችሁ የደረሳችሁበትን ለተሳታፊዎች አቅርቡ፤</u>

1. ከጉቦ ውጭ የምታውቁትን የሙስና ወንጀል ዓይነቶችን ዘርዝሩ
2. ሙስና ማለት ሌብነት ነው በሚለው ሃሳብ መስማማት አለመስማማታችሁን አስረዱ፡፡

## 1.5. የሙስና ወንጀል ምንነት

ሙስና የእንግሊዝኛውን "Corruption" የሚለውን ቃል እንዲገለጽ የምንጠቀምበት ከግእዝ የተወሰደ ቃል ነው። ለሙስና ወጥ የሆነ ትርጉም ለመስጠት አስቸጋሪ ነው። በመሆኑም የተባበሩት መንግስታት የፀረ- ሙስና ኮንቬንሽን፣ የአፍሪካ ህብረት የፀረ- ሙስና ኮንቬንሽን፣ በአውሮፓ ህብረት የፀረ- ሙስና ኮንቬንሽን እና የኢትዮጵያ የሙስና ወንጀልች ህግ፣ የፀረ-ሙስና ህጎችን ብንመረምር ለሙስና ትርጉም ከመስጠት ይልቅ የሙስና ወንጀሎች የሚባሉትን መዘርዘር ላይ ትኩረት አድርገዋል።

ከዚህ አኳያ የፀረ-ሙስና ልዩ የሥነ-ሥርዓትና ማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 236/1993 ለመጀመሪያ ጊዜ ለሙስና ወንጀል ትርጉም የሰጠና በወቅቱ በስራ ላይ በነበረዉ የ1949 የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ዉስጥ ከሚገኙ የወንጀል ድንጋጌዎች መካከል የሙስና ወንጀል ሊባሉ የሚችሉትን ያስቀመጠ ህግ ነበር። በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 2(1) ለሙስና ወንጀል የተሰጠዉ ትርጓሜ የሚከተለዉን ይመስላል፤

የሙስና ወንጀል ማለት ከመንግስት ወይም ከህዝብ አገልግሎት ወይም ከህዝብ ጥቅም ጋር በተያያዘ የሚፈጸም ማናቸዉም ወንጀል ሆኖ የተመደበበትን የመንግስት ወይም የህዝብ አገልግሎት ስራ ያለአግባብ በመጠቀም ለራስ ወይም ለሌላ ሰዉ ወይም ቡድን ጥቅም መጠየቅ፣ የተስፋ ቃል መቀበል ወይም ማግኘት ወይም ሌላዉን ሰዉ መጉዳት ሲሆን መደለያ መቀበልን፣ ጉቦን፣ የማይገባ ጥቅም መቀበልን፣በስልጣን መነገድን፣ በስልጣን ያለአግባብ መገልገልን፣ የመንግስት ስራ ወይም የህዝብ አገልግሎት ስራን ለግል ጥቅም በሚያመች አኳኋን መምራትን፣በስራ ተግባር ላይ የሚፈጸም መዉሰድና መሰወርን፣በመንግስት ስራ ላይ ሆኖ በማስገደድ መጠቀምን፣ሚስጥር ማባከንን እና የመሳሳሉትን ሌሎች ጉዳዮች ይጨምራል" የሚል ትርጉም ተሰጥቶት ነበር።

ሆኖም በዚህ አዋጅ ለሙስና ወንጀሎች የተሰጠዉ ትርጉም የተወሰኑ የሙስና ወንጀል የሚሆኑ የወንጀል አይነቶችን የዘረዘረ ቢሆንም ጉቦ መስጠትና ማቀባበል ፣ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ ይዞ መገኘት፣ በወንጀል ድርጊት የተገኘን ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብና የመሳሰሉትን የሙስና ወንጀሎች የማያካትት ከመሆኑም በላይ "... የመሳሰሉትን

ሌሎች ጉዳዮች ይጨምራል..." በሚል የተቀመጠዉ ሀረግ በክስ አቀራረብና ዉሳኔ አሰጣጥ ላይ መቋጫ የሌለዉ የትርጉም ልዩነት በዳኞች ፣በዓቃቤ ህጎች እና በጠበቆች መካከል እንዲፈጠር አድርጎ ነበር።

የ1996 የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀለ ሕግ ሲወጣ የቀድሞዉን የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ እና ልዩ የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉን በግልጽ ሽሯል። የ1996ቱ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ሕግ እንዲወጣ ምክንያት ከነበሩት ወንጀሎችስ መካከል ዋነኞቹ የሙስና ወንጀሎች እንደነበሩ በወንጀል ሕጉ ዉስጥ ተጠቅሶ እናገኛለን። ከ1996 የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ሕግ ዉስጥ በተግባር የታዩ ችግሮችን በመፍታት የተሟላ የህግ ማዕቀፍ እንዲኖር በማድረግ የፀረ-ሙስና ትግሉን ለማጠናከር እና ሀገራችን ያለባትን አህጉራዊ እና ዓለም አቀፋዊ ግዴታ በአግባቡ እንድትወጣ ለማድረግ እና በህዝባዊ ድርጅት ወይም በህዝባዉ ድርጅት ሰራተኞች፣በመንግስት የልማት ድርጅት ሰራተኞች እና በመንግስት ሰራተኞች የሚፈፀሙ ወንጀሎችን በማካተት ይዞ የወጣዉ የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 ነዉ።

**የመወያያ ጥያቄ**

<u>የሚቀጥሉትን ጥያቄዎች በቡድን ስሩና የደረሳችሁበትን ለተሳታፊዎቸ አጋሩ።</u>

1. ከተወለዳችሁበት፣ ካደጋችሁበት፣ ከተማራችሁበት እና የህይወት ልምድ ካካበታችሁበት ከኢንዱስትሪ ዘርፍ አንጻር ሙስናነ እንዴት ትፈታላችሁ?
2. 2. ሰዎች ለምን የሙስና ድርጊቶችን ኪስ እንደማውለቅና መስል የሌብነት ድርጊቶች ቆጥረዉ እራሳቸዉን ከመሰል ድርጊቶ አያቅቡም? ለምሳሌ አንደመነሻ ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር እና ተጠሪ ተቋማት ዘርፍ አኳያ የሚታየዉን ለስራ የተሰጠ የመንግስት ተሽከርካሪን ለግል ጥቅማቸው የሚያዉሉትን ግለሰቦች ጉዳይ ማንሳት ይቻላል።

## 1.6. የሙስና ዓይነቶች

የሙስና መገለጫው ብዙ አይነት ሲሆን ከትናንሽ ጥቅማ ጥቅሞች አንስቶ እስከ ከፍተኛ ገንዘብ ዝርፊያና ምዝበራ እንዲሁም ከፍተኛ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል ስልጣን አላግባብ መገልገል ሊሆን ይችላሉ። ከዚህ አንጻር ሙስና ዝቅተኛ (petty corruption)፣ ከፍተኛ (grand corruption) እና ሲስተሚክ (state capture) ሙስና ተብሎ ይከፈላል።

### 1.6.1. ዝቅተኛ ሙስና (petty corruption)

ዝቅተኛ ሙስና ከከፍተኛ ሙስና አንጻር ሲታይ በመጠኑ አነስተኛ የሆነ የህዝብና የመንግስት ገንዘብ በሙስና ዝውውር ውስጥ የሚውልበት ነው፡፡ ዝቅተኛ የሙስና ወንጀል የሚፈጸመው ከመንግስትና ከህዝብ አገልግሎት አሰጣጥና አቅርቦት ጋር በተያያዘ ሲሆን በዚህ የሙስና ወንጀል ውስጥ ተሳታፊ የሚሆኑት በቢሮክራሲው መዋቅር ውስጥ በየደረጃው አንዳንድ የመንግስት ሠራተኞችና ባለስልጣናት እንዲሁም ህገወጥ አገልግሎት ፈላጊ ግለሰቦች ናቸው፡፡

በመካከለኛና ዝቅተኛ የመንግስትና የህዝብ ተቋማት መጠኑ አነስተኛ የሆነ ገንዘብ አላግባብ የሚገኝበት ነው፡፡ መገለጫውም መለስተኛ እና ዝቅተኛ ደረጃ ላላቸው አገልግሎት አቅራቢዎች እንዲሁም ተገልጋዮች ከሚሰጥ አገልግሎት አቅርቦት (ፍቃድ መስጠት፣ ፍቃድ ማደስ፣ የትምህርትና የህክምና ማስረጃ መስጠት፣ አነስተኛ የኮንትሮባንድ እቃዎች ሳይቀረጥ ማሳለፍ የመሳሰሉት) ጋር የተያያዘ ነው፡፡ መጠኑ አነስተኛ የሆነ በአደራ የተቀበለውን ገንዘብና ንብረት መመዝበርን፣ ሰነዶችን በመሰረዝ እና በማጥፋት የማይገባ ጥቅም ማግኘትን፣ በግዢ፣ በተሽከርካሪ ጥገና ስም የማይገባ ጥቅም መውሰድን፣ አብዛኛው ህዝብ አገልግሎት ለመጠየቅ ሲሄድ የሚያጋጥመው በመሆኑ ቶሎ የሚታወቅ ህዝቡን የሚያማርር፣ በህዝቡም ትኩረት የሚያገኝ ነው፡፡

### 1.6.2. ከፍተኛ ሙስና (Grand corruption)

ከፍተኛ ሙስና በአፈጻጸሙ በአጭር ጊዜ በረቀቀና ሚስጢራዊ በሆነ ስሌት በሚሊዮን የሚቆጠር የሀገር ሀብት የሚመዘበርበት፣ ስርቆትና ማጭበርበር የሚፈጸምበት ሲሆን ከፍተኛ የፖለቲካ እና የመንግስት ባለስልጣናትና ትልልቅ ባለሀብቶች የሚሳተፉበት የሙስና አይነት ነው፡፡ ከዚህ አኳያ የተሻሻለው የፌደራል የሥ-ነምግባርና የጸረ-ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ 433/1997 " ከባድ የሙስና ወንጀል" ማለት፤-

ሀ. ከፍተኛ ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ ባላቸው የመንግስት መስሪያ ቤቶችና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ላይ የሚፈጸሙ ከፍተኛ የገንዘብ መጠንን ያካተቱ የሙስና ወንጀል ወይም

ለ. የመንግስት ባለስልጣንን የሚመለከቱ የሙስና ወንጀሎች ወይም

ሐ. በአገር ሉአላዊነት፤ኢኮኖሚ ፤ ጸጥታ እንዲሁም በህብረተሰብ ኑሮ ላይ ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርሱ ወይም ሊያደርሱ ወይም የሚችሉ የሙስናንጀሎች ናቸው በሚል ይደነግጋል፡፡

### 1.6.3. ስርዓታዊ ሙስና (systemic capture)

የሀገሪቱን አጠቃላይ የመንግስት ስርዓት መዳከምና የተደራጁ የሙስና ወንጀል ፈጻሚ ሀይሎች የመንግስትን መዋቅር ከሞላ ጎደል ተቆጣጥረው የሚገኙበትን ሁኔታ የሚያመለክት ነው፡፡ የግልጽነትና ተጠያቂነት አሰራር ከሞላ ጎደል የላላ መሆን፣ ዋና ግባቸው የዝርፊያና ምዝበራ ስራ በሆኑ የተለያዩ ከፍተኛ የፖለቲካ ቡድኖች መካከል በሚፈጠር የጥቅም ግጭት የመንግስት መዋቅሩን አንድ ሆነው ለማጥቃት የሚጠቀምበት ሁኔታ መኖሩ ነው፡፡ ሲስተሚክ ሙስና ህግ አውጪውን፣ ምርጫ አስፈጻሚውን እንዲሁም የመንግስት አስፈጻሚ መዋቅሩን የአንድ ወይም የተደራጁ የፖለቲካ ቡድኖች የዝርፊያ እና ምዝበራ ፍላጎት መጠቀሚያ በማድረግ ይገለጻል፡፡

ከፍተኛ ሙስና ስር ሲሰድ ስርአታዊ (systemic capture) በመሆን መንግስትን ሊቆጣጠር (state capture) ሊሆን የሚችል ነው፡፡

### 1.6.4. ፖለቲካዊ ሙስና (political Corruption)

በፖለቲካ ፓርቲዎች፣ በማንኛውም ደረጃ የፖለቲካ ውሳኔ በሚሰጡ ከፍተኛ የፖለቲካ አመራር አካላትና በመንግስት ባለስልጣናት በውሳኔ አሰጣጥ ላይ የሚፈጸም የሙስና ወንጀል ነው፡፡ ፖለቲካዊ ሙስና ብዙ ጊዜ ፖለቲካዊ ውሳኔዎች ለግልና ለቡድን ጥቅም በሚያመች መንገድ መወሰንን ወይም እንዲወሰኑ ማድረግንና የአንድን ማህበረሰብ ዱሞክራሲያዊ ሥርዓት፣ እሴቶችንና ልማዶችን የመጣስ ማንኛውንም ተግባር የሚመለከት ነው፡፡

ፖለቲካዊ ሙስና በተለያዩ መልኮች የሚገለጽ ቢሆንም ጎልተው የሚታዩ ዋና ዋናዎቹ የፖለቲካዊ ሙስና ዓይነቶች በምርጫ ወቅት የሚፈጸም ሙስና (Electoral Corruption)፣ የመንግስት ቢሮክራሲንና የመንግስት ሥራን ለፖለቲካ ጥቅም ማዋል (Politicization of bureaucracy) እንዲሁም በህግ አወጣጥ ሂደት ላይ የሚፈጸም ሙስና (Corruption in the legislative process) ናቸው፡፡

በአጠቃላይ በየተቋሙ የሚፈጸሙ የሙስና አይነቶች እንደየተቋማቱ አገልግሎት አሰጣጥ እና ተልዕኮ የሚለያዩ ናቸው፡፡

***የመወያያ ጥያቄዎች***

<u>በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ በጥንድ ከተወያያችሁ በኋላ የደረሳችሁበትን ለተሳታፊዎቸ አቅርቡ፡፡</u>

1. በኢንዱስትሪ ዘርፍ ውስጥ የሚከሰቱት ሙስናዎች በአብዛኛዉ በየትኛው የሙስና አይነት ስር ይመደባሉ?

2. ከዚህ በታች የቀረቡት ሶስት የሙስና ናሙናዎች በኢንዱስትሪ ዘርፍ ዉስጥ እንዴት እንደተፈጸሙ የሰማችሁትን ለተሳታፊዎች አቅርቡ፡፡

3. በኢንዱስትሪ ዘርፍ የተከሰቱ ሙስና i፣ ii እና iii ከየትኞቹ የሙስና ዓይነቶች ሰር ይመደባሉ? አብራሩ፡፡

**ሙስና** i፦ የተሰጠን ሃላፊነት በመጠቀምና አላስፈላጊ ጥቅም በመውሰድ ተመሳሳይ ምርት ከሚያመርቱ አምራቾች ጥቅም ያገኙበትን አምራች ገበያ እንዲያገኝ በማድረግ ሌሎችን ከገቢያ ውጭ ማድረግ፤

**ሙስና** ii፦ ለስራ የተሰጠ የመንግስት ተሸከርካሪን ለግል ጥቅም ማዋል፤

**ሙስና** <u>iii</u>፦ ከ<u>መንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥ (EGP-Electronic Government Procurement)</u> ግዥ ጋር ተያይዞ ባለው Re-submission የሚለውን ለፈለጉት ሰው በመክፈት እና ላልፈለጉት ሰው በመዝጋት የመንግስትን ጥቅም መከልከል፡፡

## 1.7. የሙስና ወንጀል ልዩ ባህርያት

የሙስና ወንጀል ነባር ከሚባሉት የወንጀል አይነቶች የተለየና ዉስብስብ ሆነ ወንጀል፡፡ የዚህን ወንጀል ከሌሎች የተለመዱ ወይም ነባር ወንጀሎች የተለየ የሚያድርጉትን ልዩ ሁኔታዎች ማወቅ የሙስና ወንጀልን ለመመርመር ፣ለማጋለጥ ለመክሰስና አጥፊዎችን ለመቅጣት አስቸጋሪ እንዲሆን የሚያድርጉትን ሁኔታዎች ለመረዳትና የተለየ ስልት ለመቀየስ ይረዳሉ፡፡

የሙስና ወንጀል ነባር ከሚባሉት የወንጀል አይነቶች ልዩ ከሚያደርጉት መካከል የሚከተሉት ሊጠቀሱ ይችላሉ።

### 1.7.1. የወንጀሉ አፈጻፀም ስልት

የሙስና ወንጀል በስሜት አልያም በጥላቻ ሳይሆን በሚስጢር፣ በስምምነት፣ በጥንቃቄ፣ እንዲሁም ጥቅም ለማግኘት የሚፈጸም ነዉ። በዚህም ምክንያትም መፈፀሙን ለማወቅ የሚያችል ምንም አይነት ምልክት ማግኘት አዳጋች ነዉ። የሙስና ወንጀሎች በአብዛኛዉ የሚፈጸሙት በዘርፉ እዉቀት ባላቸዉ ባለሙያዎች ነዉ። ከዚህ በተጨማሪም በሚስጥር፣ በጥንቃቄ፣ እንዲሁም በቴክኖሎጂ በመታገዝ መፈፀሙ ብቻ ሳይሆን አጥፊዉ ለምርመራ መነሻ ሊሆን የሚችል ማስረጃ የማጥፋት አቅም ስላዉ ከነባር ወንጀሎች ለየት ያደርገዋል።

### 1.7.2. የሙስና ወንጀል የሚስከትለዉ ጉዳት

የሙስና ወንጀል የማይገባ ጥቅምን በማስገኘትና በማካበት፣ የማይገባ መብትን በመስጠት፣ ሌሎችን የሚገባቸዉን ሀብት በማጉደል ወይም መብታቸዉ ላይ በደል በማድረስ በዋናነት ፍትሀዊነት መጓደልን ያስከትላል ። ለአንዱ ያለግባብ ፈቃድ ወይም መብት በመስጠት ሌሎችን በመንፈግ በዜጎች እና በሰዎች መካከል ሊኖር የሚገባዉን እኩልነት ያጠፋል። ከዚህ ባለፈም በአንድ ሀገር ሊኖር የሚገባ ማህበራዊ ፍትህ ወይም ፍትሀዊ የሀብት ክፍፍልን ያጠፋል። ዜጎችና እና ልማት የሚገባቸዉ የህብረተሰብ ክፍሎች የሚገባቸዉ መሠረታዊ አገልግሎት በጊዜና በጥራት እንዳይደረሳቸዉ ያደርጋል። በአጠቃላይ የሙስና ወንጀል ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ዘርፈ ብዙ ችግሮችን ያደርሳል።

### 1.7.3. የወንጀል ፈጻሚዎች አቅም

የሙስና ወንጀልን የሚፈጽሙት የመንግስት ሰራተኞችና ባለስልጣኖች የተሰጣቸውን ስልጣን መከታ አድርገው ሲሆን እነዚህ የመንግስት ሰራተኞች ግዴታቸውን እንዲጥሱ ለመንግስት ባለስልጣን በማማለያነት ጥቅም በመስጠትና አፍ በማዘጋት በወንጀሉ ተሳታፊ የሚሆኑ አላግባብ የመበልጸግ ፍላጎት ያላቸው ባለሀብቶች ለዚህ አላማ የሚያውሉት ሀብት ወይም ገንዘብ መኖሩ ነው። እነዚህ የመንግስት ባለስልጣንና አላግባብ በዝርፊያ መበልጸግ የሚፈልጉ ባለሀብቶች በእጃቸው ያለው ስልጣንና ገንዘብ የሙስና ወንጀሉ እንዳይመረመርና እንዲደበቅ

ለማድረግ አቅም የሚሰጣቸው ነው። ወንጀሉን ለማጋለጥ የሚፈልጉትን በማባበል እንቢ ካሉም በማስፈራራትና የበቀል እርምጃ በመውሰድ ጉዳዩ እንዳይጋለጥ ለማድረግና ተድበስብሶ እንዲቀር ለማድረግ የሚያስችል አቅም አላቸው። በእንዲህ አይነት ሁኔታ ውስጥ የሙስና ወንጀልን ማጋለጥ፣ መመርመርና አጥፊዎችን ለህግ አቅርቦ ማስቀጣት ከባድ ነው።

### 1.7.4. በወንጀሉ ቀጥተኛ ተጎጂ ግለሰብ አለመኖር

የተለመዱ ወይም ነባር በሚባሉት ወንጀሎች አጥቂና ተጠቂ ይኖራል። ከወንጀሉ ሁለቱም ተጠቃሚ ስለማይሆኑ አጥቂ የፈጸመዉን የወንጀል ድርጊት ተጠቂ የደረሰበትን በደል ለመካስ ስለሚያጋልጠዉ ወንጀሉን ለመመርመርና አጥፊዉን ለማስቀጣት ብዙም ችግር ላይገጥም ይችላል። በሙስና ወንጀል ግን ሁለቱም ተዋንያን ከወንጀሉ ተጠቃሚ ሊሆኑ ወይም በመንጀል ድርጊቱ ሊረኩ ይችላሉ። በወንጀሉ የተጠቀመ ወይም የረካ ሰዉ ደግሞ መደበቁን ይገፋበታል እንጂ ሊያጋልጥ አይችልም። ስለሆነም በዚህ ምክያት የሙስና ወንጀል ከመደበኛ ወይም ነባር ከሚባሉት የወንጀል አይነቶች በእጅጉ ይለያል።

“የሁሉም የሆነ የማንም አይደለም” የሚል አባባል አለ። የሙስና ወንጀል በቀጥታ በአንድ ግለሰብ ወይም ቡድን ላይ የሚደርሰዉ ጉዳት ላይኖር ይችላል። በአንጻሩ በአገርና በዝዝብ ላይ የሚያደርሰዉ ጉዳት ግን እጅግ ከፍተኛ ነዉ። በዚህ ምክንያት ግለሰብ ወይም ቡድን በቀጥታ ተጠቂ ስለማይሆን ወንጀሉ ተፈጽሞ እንኳ ቢገኝ ያገባኛል ወይም የኔ ጉዳይ ነዉ ብሎ ጉዳዩን ለህግ የሚጠቁም እና አስፈላጊዉን ማስረጃ በማቅረብ እንዲመረመርና አጥፊዎች እንዲቀጡ የሚያደርግ ሰዉ ላይገኝ ይችላል። በዚህም ምክንያት ወንጀሉ ሳይጣራ ተዳፍኖ የሚቀርበት አጋጣሚ እጅጉ ብዙ ነዉ።

### 1.7.5. ድንበር ተሻጋሪነቱ

ሰዎች የሙስና ወንጀለ የሚፈጽሙበት ዋነኛ ምክንያት ተገቢ ባልሆነ መንገድ ሀብትና ንብረት ለማፍራት ነዉ። በህገወጥ መንገድ የሚገኝ ሀብትና ንብረት ደግሞ ከፍተኛ በሚሆንበት ጊዜ ከአገር አልፎ ወደሌሎች አገሮች የመጓዝ አቅም ከመፍጠሩም በላይ እንደሽብርተኝነት ለመሳሰሉ ሌሎች ድንበር ተሻጋሪ ወንጀሎች መፈጠር አጋዥ በመሆኮን ሊጊሊግል ይችላል። ይህ ወንጀል ድንበር ተሻጋሪ በሚሆንበት ጊዜ ወንጀሉ ከአለም አቀፍ ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች ጋር ትስስር

በመፍጠር ህጋዊ ሽፋን ተላብሶ ሊፈጸም ስለሚችል የወንጀል አፈጻጸሙን ስልት ዉስብስብ ያደርገዋል፡፡

## 1.8. በአዋጅ ቁጥር 881/2007 የተደነገጉ የሙስና ወንጀሎች

የፀረ-ሙስና ልዩ የሥነ-ሥርዓትና ማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 236/1993 ለመጀመሪያ ጊዜ ለሙስና ወንጀል ትርጉም የሰጠና በወቅቱ በስራ ላይ በነበረዉ የ1949 የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ዉስጥ ከሚገኙ የወንጀል ድንጋጌዎች መካከል የሙስና ወንጀል ሊባሉ የሚችሉትን ያስቀመጠ ህግ ነበር፡፡ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 2(1) ለሙስና ወንጀል የተሰጠዉ ትርጓሜ የሚከተለዉን ይመስላል፦

የሙስና ወንጀል ማለት ከመንግስት ወይም ከህዝብ አገልግሎት ወይም ከህዝብ ጥቅም ጋር በተያያዘ የሚፈጸም ማናቸዉም ወንጀል ሆኖ የተመደበበትን የመንግስት ወይም የህዝብ አገልግሎት ስራ ያለአግባብ በመጠቀም ለራስ ወይም ለሌላ ሰዉ ወይም ቡድን ጥቅም መጠየቅ፣ የተስፋ ቃል መቀበል ወይም ማግኘት ወይም ሌላዉን ሰዉ መጉዳት ሲሆን መደለያ መቀበልን፣ ጉቦን፣ የማይገባ ጥቅም መቀበልን፣በስልጣን መነገድን፣ በስልጣን ያለአግባብ መገልገልን፣ የመንግስት ስራ ወይም የህዝብ አገልግሎት ስራን ለግል ጥቅም በሚያመች አኳኋን መምራትን፣በስራ ተግባር ላይ የሚፈጸም መዉሰድና መሰወርን፣በመንግስት ስራ ላይ ሆኖ በማስገደድ መጠቀምን፣ሚስጥር ማባከንን እና የመሳሳሉትን ሌሎች ጉዳዮች ይጨምራል የሚል ትርጉም ተሰጥቶት ነበር፡፡

ሆኖም በዚህ አዋጅ ለሙስና ወንጀሎች የተሰጠዉ ትርጉም የተወሰኑ የሙስና ወንጀል የሚሆኑ የወንጀል አይነቶችን የዘረዘረ ቢሆንም ጉቦ መስጠትና ማቀባበል ፣ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ ይዞ መገኘት፣ በወንጀል ድርጊት የተገኘን ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብና የመሳሰሉትን የሙስና ወንጀሎች የማያካትት ከመሆኑም በላይ *"... የመሳሰሉትን ሌሎች ጉዳዮች ይጨምራል..."* በሚል የተቀመጠዉ ሀረግ በክስ አቀራረብና ዉሳኔ አሰጣጥ ላይ መቋጫ የሌለዉ የትርጉም ልዩነት በዳኞች ፣በዓቃቤ ህጎች እና በጠበቆች መካከል እንዲፈጠር አድርጎ ነበር፡፡

ከ1996 የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ሕግ ዉስጥ በተግባር የታዩ ችግሮችን በመፍታት የተሟላ የህግ ማዕቀፍ እንዲኖር በማድረግ የፀረ-ሙስና ትግሉን ለማጠናከር እና ሀገራችን ያለባትን አህጉራዊ እና ዓለም አቀፋዊ ግዴታ በአግባቡ እንድትወጣ ለማድረግ እና በህዝባዊ ድርጅት ወይም በህዝባዉ ድርጅት ሰራተኞች፣በመንግስት የልማት ድርጅት ሰራተኞች እና በመንግስት ሰራተኞች የሚፈፀሙ ወንጀሎችን በማካተት ይዞ የወጣዉ የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 ነዉ

የሙስና ወንጀል ድንጋጌዎች በአዋጅ ቁጥር 881/2007 ላይ ከአንቀጽ 9 እስከ 33 ላይ ተመልክቷል፡፡ በህጉ አወቃቀር መሠረት የሙስና ወንጀል ተብለው የተለዩት በ25 አንቀፆች የተጠቃለሉ ጉዳዮች ብቻ ናቸው፡፡

### 1.8.1. በሥልጣን ያለአግባብ መገልገል (አንቀፅ 9)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ የማይገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ወይም በሌላ ሰው ጥቅም ወይም መብት ላይ ጉዳት እንዲደርስ ለማድረግ በማሰብ፤ የተሰጠውን ሹመት፣ ሥልጣን ወይም ኃላፊነት በግልፅ ተግባር(በማድረግ) ወይም በግድፈት(ባለማድረግ) ያለአግባብ የተገለገለበት እንደሆነ፤
በግልፅ ከተሰጠው ሥልጣን ወይም ኃላፊነት አሳልፎ የሠራ እንደሆነ፤ ወይም
ሥልጣን ወይም ኃላፊነት ሳይኖረው ወይም ከሥራው ከታገደ፣ ከተዛወረ፣ ከተሻረ ወይም ሥልጣኑን ወይም ኃላፊነቱን ከተወ በኋላ የሠራበት እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠቃል፡፡

### 1.8.2. ጉቦ መቀበል (አንቀፅ 10)

ማንኛዉም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በኃላፊነቱ ወይም በሥራ ግዴታዉ ማድረግ የማይገባዉን ለማድረግ ወይም ማድረግ የሚገባዉን ላለማድረግ በቀጥታም ወይም በተዘዋዋሪ ለራሱ ወይም ለሌላ ሰዉ ጥቅም እንዲሰጥ ጠየቀ ፣የተቀበለ እንደሆነ  በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

### 1.8.3. የማይገባ ጥቅም መቀበል (አንቀፅ 11)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በተሰጠው ኃላፊነት መሠረት ማድረግ የሚገባውን ተግባር ለማከናወን ሲል ይህንኑ ተግባር ከመፈፀሙ በፊት ወይም ከፈፀመ በኋላ ጥቅም እንዲሰጠው የጠየቀ፣ ያገኘ ወይም የተስፋ ቃል የተቀበለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

### 1.8.4. አስታራቂ ሽማግሌዎችና ሌሎች ሰዎች የሚፈፅሙት ጉቦ የመቀበል ወንጀል (አንቀጽ 12)

ማንኛዉም አስታራቂ ሽማግሌ ፣የግልግል ዳኛ፣ የፍርድ ቤት ነባሪ ፣ ንብረት ጠባቂ ፣ወይም አጣሪ ፣ሥራዉን ለማካሄድ በባለስልጣን የተሾመ ተርጓሚ ወይም አስተርጓሚ ወይም በዳኝነት ወይም በዳኝነት ነክ በሚታይ ጉዳይ ላይ በሙያዉ ረገድ አስተያየቱን ወይም የምስክርነት ቃሉን

የሚሰጥ ማንኛዉም ልዩ አዋቂ (ኤክስፐርት) ፣ወይም ገቢና ወጪን ኦዲት የሚያደርግ ኦዲተር፣ ወይም ግንባታ በተገባዉ ዉል መሰረት መከናወኑን የሚረጋግጥ መሃንዲስ ማድረግ የሚገባዉን ላለማድረግ ወይም ማድረግ የሚገባዉን ለማድረግ ጉዳ ከሚመለከተዉ ሰዉ ላይ ጥቅም እንዲሰጠዉ የጠየቀ ወይም ተቀበለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

### 1.8.5. የመንግስት ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ስራን በማያመች አኳኋን መምራት (አንቀጽ 13)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ የማይገባ ጥቅም ለማግኘት፣ ወይም ለማስገኘት በማሰብ ሥልጣኑን ወይም ሃላፊነቱን ተጠቅሞ፦

በንግድ ወይም በሌላ ሥራ፣ በግዢ ወይም በሽያጭ ወይም ከሚያከናውነው ሥራ ጋር በተያያዘ በማናቸውም የሥራ ግንኙነት ማናቸዉንም ዓይነት ጥቅም የወሰደ ወይም ይህን ጥቅም የሚያገኝበትን ውል የተዋዋለ፤ ወይም ሌላ ዘዴ የፈጠረ እንደሆነ፤

አግባብ ባለው ባለስልጣን ወይም ኃላፊ ከተወሰነው በላይ በሆነ ዋጋ የዕቃ ማቅረብ ውል፣የሥራ መቋረጥ ውል ወይም ማናቸውም የሥራ ውል የተዋዋለ ወይም በዉል ከተመለከተው ዕቃ ወይም አገልግሎት ውጭ የተቀበለ እንደሆነ፤

በጠቅላላዉ በሥራዉ ሥልጣን ወይም ኃላፊነት መሠረት በአደራ የተሰጠዉን ወይም ሊጠብቀዉና ሊከላከለዉ የሚገባዉን የመንግስት መስሪያ ቤት፣ የመንግስት የልማት ድርጅት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ጥቅም የሚጎዳ ተግባር በማናቸዉም ዘዴ የፈፀመ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

### 1.8.6. አደራ በተሠጠው ዕቃ ያለአግባብ ማዘዝ (አንቀፅ 14)

ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ በሕግ አግባብ ሳይፈቀድለትና የግል ንብረት ለማድረግ በማሰብ ሳይሆን ታሽጎ የተረከበዉን ጥቅል፣ ኢንቨሎፕ፣ ሰነድ፣ ባለዋጋ ነገር፣ ወይም እንደታሸገ የተረከበውን ማናቸውንም ዕቃ፦

የከፈተ፣ ያስከፈተ፣ የወሰደ ወይም ያስወሰደ ወይም የእሽጉን ይዘት የገለጠ ወይም ዕቃውን አሳልፎ የሰጠ እንደሆነ፤ ወይም

የተገለገለበት ወይም ሌላ ሰው እንዲገለገልበት የፈቀደ እንደሆነ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

### 1.8.7. በሥራ ተግባር የሚፈፀም የመውሰድና የመሰወር ወንጀል (አንቀፅ 15)

የማይገባ ቁሳዊ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ ማንኛዉም ፦

የመንግሥት ሠራተኛ በብርበራ፣ በመያዝ፣ በመውረስ ሥርዓት፣ በሐራጅ ሽያጭ፣ በህግ ውርስ ወይም ፍርዱ በንብረቱ ላይ እንዲፈፀም በመወሰኑ ወይም ይህን የመሰለ ማናቸውም ሥራ በሚያከናውንበት ወይም በሚያስፈፅምበት ጊዜ፤ ወይም

የመንግሥት ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በማንኛውም የሥራ አጋጣሚ በእጁ ሊገቡ የቻሉትን ወይም በአደራ የተረከባቸውን ወይም የሚጠብቃቸውን፤ ዕቃዎችን፣ ሰነዶችን፣ ባለዋጋ ነገሮችን፣ጥሬ ገንዘቦችን፣ ተንሳቃሽ ወይም አላቂ ዕቃዎችን የወሰደ ወይም የሰወረ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል።

### 1.8.8. በሥልጣን ወይም በኃላፊነት መነገድ (አንቀፅ 16)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በሥራው ምክንያት ባለው ወይም አስመስሎ ባቀረበው ተሰሚነት፦

አግባብ ባለው ባለስልጣን ወይም ኃላፊ ተወስኖ የሚሰጥ የሥራ ደረጃ፣ ሹመት፣ ሥራ ፣ ሽልማት፣ የአገልግሎት ዋጋ፣ ልዩ ችሮታ፤

በቁጥጥሩ ወይም በአመራሩ ሥር በሚገኙ ባለስልጣኖች፣ኃላፊዎች ወይም የአስተዳደር ክፍሎች የሚደረግ ዉል፣የንግድ ስምምነት፣የስራ ጨረታ፣የዕቃ ማቅረብ ዉል ፣ወይም ሌላ ጥቅም ወይም
በአጠቃላይ ከአንድ ባለስልጣን ፣ኃላፊ ወይም የአስተዳደር ክፍል የሚሰጠዉን ጥቅም ወይም የሚረዳ ዉሳኔ፣ ለሌላ ሰዉ ለማስገኘት ስጦታ ወይም ሌላ ጥቅም የጠየቀ ወይም የተቀበለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል።

### 1.8.9. በህገወጥ መንገድ መሰብሳብ ወይም ማስረከብ (አንቀፅ 17)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ የማይገባ ጥቅም ለራሱ ለማግኘት በማሰብ፦

ሊከፈል የማይገባ መሆኑን ወይም በህግ ከተወሰነው ታሪፍ በላይ መሆኑን እያወቀ ቀረጥ፣ ግብር፣ ልዩ ልዩ ገቢ ወይም ልዩ ልዩ የገቢ ጥቅም ፣ ምንዳ፣ ደመወዝ፣ ካሳ ወይም ሌላ ወጪ የሰበሰበ ወይም እንዲሰበሰብ ያዘዘ እንደሆነ፤

ማናቸውንም ዕቃ ወይም ክፍያ በሚያስረክብበት ወይም በሚሰጥበት ጊዜ ማስረከብ ወይም መክፈል ከሚገባው አሳንሶ ያስረከበ ወይም የከፈለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠቃል፡፡

### 1.8.10. ያለአግባብ ጉዳይን ማጓተት (አንቀፅ 18)

ማንኛዉም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በኃላፊነቱ ወይም በሥራዉ ምክንያት በቀረበለት ጉዳይ ላይ ጥቅም ካለዉ ማንኛዉም ሰዉ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ጥቅም ለማግኘት ፣በጉዳዩ ላይ ጥቅም ያለዉን ማንኛዉንም ወገን ለመጥቀም ወይም ለመጉዳት ሲል ከህግ፣ ከሥራ ደንብ፣ ወይም ከመመሪያ ወይም ከተለመደዉ አሠራር ዉጭ ያለ በቂ ምክንያት ያልወሰነ ፣ያዘገየ ወይም ባለጉዳዩን ጉላላ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

### 1.8.11. ዋጋ ያለውን ነገር ያለክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ ማግኘት (አንቀፅ 19)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ተገቢ ምክንያት ሳይኖረው ያለክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ ማናቸውንም ዋጋ ያለውን ነገር የተቀበለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ይጠየቃል፡፡

ሁለተኛዉ በዚህ አንቀፅ የሚያስቀጣዉ ድርጊት ንብረትን፣ የፋይናንስ አቋምን፣ ስጦታ መቀበልን ማስመዝገብ ወይም ማሳወቅ እንደሚገባ በህግ ወይም በደንብ በተደነገገ ጊዜ አለማሳወቅ በተመሳሳይ ያስቀጣል፡፡

በአገሩ ወይም በአካባቢው ባህል ወይም ልማድ መሠረት እንደተራ የወዳጅነት ምልክት የሚሰጥ ዋጋ ያለው ሥጦታ መቀበል ወይም ከስጋ ወይም ከጋብቻ የቅርብ ዘመድ ወይም የቅርብ ወዳጅ ስጦታ ማግኘት አያስጠይቅም፡፡

### 1.8.12. ያለአግባብ ፍቃድ መስጠት ወይም ማፅደቅ (አንቀፅ 20)

ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ ሆነ ብሎ ወይም በቸልተኝነት፣ብቁ ላልሆነ ወይም በህግ ሊሰጠው ለማይገባ ሰው ማናቸውንም የንግድ ወይም የሥራ ፈቃድ የሰጠ ወይም ያፀደቀ

ወይም እንደሆነ፣ ወይም አንድ ነገር የሚከናወንበትን ቦታ ያለአግባብ የፈቀደ ወይም የሰጠ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

### 1.8.13. ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ (አንቀፅ 21)

ማንኛዉም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ የሆነ ወይም የነበረ ሰዉ የኑሮ ደረጃዉ አሁን ባለበት ወይም አስቀድሞ በነበረበት የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሥራ ወይም በሌላ መንገድ ከሚያገኘዉ ወይም ሲያገኘዉ ከነበረዉ ህጋዊ ገቢ የበለጠ እንደሆነ፤ ያለዉ ንብረት ወይም የገንዘብ ምንጭ አሁን ባለበት ወይም አስቀድሞ በነበረበት የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሥራ ወይም በሌላ መንገድ ከሚየገኘዉ ወይም ሲያገኘዉ ከነበረዉ ህጋዊ ገቢ ጋር የማይመጣጠን እንደሆነ በሙስና መንጀል ያስጠይቃል፡፡

### 1.8.14. የሥራ ሚስጥርን መግለፅ (አንቀፅ 22)

አግባብነት ባለዉ ህግ አያስጠይቅም ተብሎ የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛዉም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት ፣ለሌላ ሰዉ ለማስገኘት ወይም በሌላ ሰዉ ጥቅም ወይም መብት ላይ ጉዳት እንዲደርስ ለማድረግ በማሰብ በሥራዉ ምክንያት ያወቀዉ ሆኖ በጠባዩ ሚስጥር የሆነዉን ወይም በሚስጥር እንዲጠበቅ የታዘዘዉን ወይም ለህዝብ እንዳይገለጽ የተከለከለዉን መረጃ ፣ሰነድ ወይም ፍሬ ነገር ሥራዉን ወይም ሹመቱን ከለቀቀ በኋላ ቢሆንም እንኳ የገለጸ ወይም የስተላለፈ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

### 1.8.15. መንግሥታዊ ወይም የህዝባዊ ሰነዶችን አስመስሎ ማዘጋጀት፣ ወደ ሐሰት መለወጥ ወይም በሐሰተኛ ሰነድ መገልገል (አንቀፅ 23)

ማንኛዉም ሰው የሌላዉን ሰዉ መብት ወይም ጥቅም ለመጉዳት ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ተገቢ ያልሆነ ማናቸውንም መብት ወይም ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ታስቦ የሚፈፀም ነዉ፤

አንድ ፅሁፍ፣ መዝገብ ወይም ማንኛውንም ሰነድ የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት በማስመሰል ያዘጋጀ ወይም የፈጠረ እንደሆነ፤

በመንግሥት ወይም በህዝባዊ ድርጅት መዝገብ ፣ፅሁፍ ወይም ሰነድ የሰፈረን እውነተኛ ፅሁፍ በመለወጥ ወይም በመደለዝ፣ በሐሰተኛ ፊርማ፣ በእጅ በተደረገ ምልክት ወይም በጣት ፊርማ፣ በማህተም ወይም የሌለውን ሥልጣን ወይም ችሎታ እንዳለው አስመስሎ በመፈረም ሐሰተኛ ሰነድ የፈጠረ፤ ወደ ሐሰት በተለወጠ ወይም በሐሰት በተዘጋጀ ሰነድ እያወቀ የተገለገለበት እንደሆነ፤ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

### 1.8.16. መንግስታዊ ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሰነዶችን ማጥፋት ወይም ጉዳት ማድረስ (አንቀፅ 24)

ማንኛዉም ሰዉ የሌላዉን ሰዉ መብት ወይም ጥቅም ለመጉዳት ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰዉ ተገቢ ያልሆነ ማናቸዉንም መብት ወይም ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ በመንግስት ወይም በህዝባዊ ድርጅት ወይም በህዝብ ሰነድ ላይ ጉዳት እንዲደርስበት ያደረገ ፣ የቀደደ፣ ያጠፋ ፣ጥቅም ላይ እንዳይዉል ያደረገ ወይም የወሰደ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠቃል፡፡

### 1.8.17. ዋጋ ያለዉን ነገር ያለክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ መስጠት (አንቀፅ 26)

ማንኛዉም ሰዉ ተገቢ ምክንያት ሳይኖረዉ ለማንኛዉም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ወይም ከእርሱ ጋር ግንኙነት ላለዉ ማንኛዉም ሌላ ሰዉ ያለክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ ማናቸዉንም ዋጋ ያለዉ ነገር ያቀረበ ፣የሰጠ ወይም ለመስጠት የተስማማ እንደሆነ ያስጠይቃል፡፡

በአገሩ ወይም በአካባቢዉ ባህል ወይም ልማድ መሰረት እንደተራ የወዳጅነት ምልክት የሚሰጥ ዋጋ ያለዉ ስጦታ መስጠት ወይም ለስጋ ወይም ለጋብቻ የቅርብ ዘመድ ወይም ለቅርብ ወዳጅ ስጦታ መስጠት አያስጠቅም፡፡

### 1.8.18. ጉቦ ወይም ተገቢ ያልሆነ ጥቅም መስጠት (አንቀፅ 25)

ማንኛዉም ሰዉ አንድ የመንግስት ሠራተኛ ወይም የህዝባዉ ድርጅት ሠራተኛ በኃላፊነቱ ወይም በስራ ግዴታዉ ማድረግ የማይገባዉን እንዲያደርግ ወይም ማድረግ የሚገባዉን እንዳያደርግ ጥቅም ወይም ስጦታ የሰጠ ወይም ያቀረበ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

### 1.8.19. ማቀባበል (አንቀፅ 27)

ማንኛዉም ሰዉ ለራሱ ማናቸዉንም ዓይነት ጥቅም ባያገኝም እንኳ የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሥራን ለሚያከናዉን ሰዉ ጉቦ ለመስጠት ገንዘብ ፣ዋጋ ያለዉ ነገር ፣ አገልግሎት ወይም ሌላ ዓይነት ጥቅም ከሌላ ሰዉ የተቀበለ እንደሆነ፤ ወይም የራሱን የባንክ ሂሳብ እንደዚህ ዓይነት ጉቦ ለማቀባበል ያዋለ እንደሆነ፤ ወይመ ጉቦ እንዲሰጣጡ ሁኔታዎችን ያመቻቸ ፣ያገናኘ ፣ ያስማማ ወይም የደለለ እንደደሆነ በሙስና ወንጀል ይጠየቃል፡፡

### 1.8.20. በሌለው ሥልጣን መጠቀም (አንቀፅ 28)

ማንኛውም ሰው ከመንግሥት ወይም ከህዝባዊ ድርጅት ሥራው ከታገደ፣ ከተዛወረ፣ ከተሻረ፣ ከተወገደ ወይም ሥልጣኑን፣ ኃላፊነቱን ከተወ በኂላ በሥራው ላይ ያለ በማስመሰል፤ለወደፊቱ የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ እሆናለሁ ብሎ በማሳመን ወይም ሠራተኛ ሳይሆን መስሎ በመቅረብ፤

ይህንን አደርጋለሁ በማለት የተስፋ ቃል በመግባት ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ወይም ሥጦታ ከሌላ ሰው የጠየቀ፣ የተቀበለ እንደሆነ ይጠየቃል፣

### 1.8.21. በግል ተሰሚነት መነገድ (አንቀፅ 29)

ማንኛውም ሰው የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ ባይሆንም በሰዎች ዘንድ ያለውን ወይም እንዳለው ያስመሰለውን ተሰሚነት በመጠቀም በአንድ የመንግስት ወይም በህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ብቻ ሊሰጥ የሚችለውን ልዩ መብት ወይም ጥቅም እኔ አደርግልሀለሁ

በማለት ለሌላ ሰው ለማስገኘት ሲል ገንዘብ፣ ስጦታ፣ሌላ ጥቅም የጠየቀ፣ የተቀበለ ወይም የተስፋ ቃል የተቀበለ እንደሆነ፤ በሙስና ይጠየቃል።

ሰጭዉም ቢሆን የህግ ተጠያቂነት አገልግሎቱ የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ ብቻ እንደሚሰጥ እያወቀ ልዩ መብት ወይም ጥቅም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ ገንዘብ፣ ስጦታ፣ ሌላ ጥቅም የሰጠ፣ ለመስጠት የተስማማ እንደሆነ ይጠየቃል፣

## 1.8.22. በምርጫ ላይ የሚሰጥ መደለያ (አንቀጽ 30)

ማንኛውም ሰው የመምረጥ ወይም የመመረጥ መብት ያለው ሌላ ሰው በመብቱ በተወሰነ መንገድ እንዲጠቀም ወይም መብቱን እነዲተው ለማድረግ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ገንዘብ ወይም በማናቸውም ሌላ አይነት ጥቅም የሰጠ፣ ወይም ለመስጠት ቃል የገባ እንደሆነ፣ በሙስና ወንጀል ይጠየቃል።

## 1.8.23. ከባድ የእምነት ማጉደል (አንቀፅ 31)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ተገቢ ያልሆነ ብልፅግና ለራሱ ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት የሆነውንና ለአንድ ለተወሰነ አገልግሎት ወይም በአደራ የተሰጠውን ዋጋ ያለውን ነገር፣ ጥሬ ገንዘብ በሙሉ ወይም በከፊል ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ያደረገ፣ የወሰደ፣ ያስወሰደ፣ የሰወረ ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው አገልግሎት ያዋለ፤መዉሰዱ፣ ማስወሰዱ ወዘተ በህግ ግምት የሚጣል በመሆኑ ዐቃቤ ህግ ንብረቱ መጉደሉን እንጂ መዉሰድ ማስወሰዱን ማስረዳት አይጠበቅበትም።

## 1.8.24. ከባድ አታላይነት (አንቀፅ 32)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ተገቢ ያልሆነ ብልፅግና ለራሱ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰዉ ለማስገኘት በማሰብ አሳሳች የሆኑ ነገሮችን በመናገር፣ የራሱን ማንነት ወይም ሁኔታ በመሰወር ወይም መግለፅ የሚገባውን ነገር በመደበቅ ወይም የሌላውን

ሰው የተሳሳተ እምነት ወይም ግምት በመጠቀም፣ በማድረግም ሆነ ባለማድረግ ሌላውን ሰው ማታለል በህግ የሚያስቀጣ ነዉ፡፡

### 1.8.25. በሙስና ወንጀል የተገኘን ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብና በወንጀሉ ስለመርዳት (አንቀጽ 33)

በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ህጋዊ አስመስሎ የማቅረብ ወንጀል የተፈጸመው በሙስና ወንጀል አመንጪነት ከሆነ አግባብነት ያለው በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብ ህግ ተፈጻሚነት እንደተጠበቀ ሆኖ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

**የመወያያ ጥያቄ**

የኢንዱስቲሪ ሚኒስቴር (2016 ዓ/ም) ባደረገዉ ጥናት መሰረት ያልተገባ ጥቅም በማሰብ በአንድ ርዕሰ ጉዳይ ተመሳሳይ ጥናት ማድረግ፣ የሌላን የምርምር ዉጤት እንደ ራስ አስመስሎ ማቅረብ፣ ከዚህ በፊት የተጠኑ ጥናቶችን አዲስ አስመስሎ ማቅረብ፣ በቡድን የተሰራ ጥናት የግል አስመስሎ ማቅረብና ችግር ፈቺ ያልሆነ ጥናት እና ምርምሮችን ማቅረብ በዘርፉ የታዩ የሙስና ድርጊቶች መሆናቸዉን ያመላከተ ሲሆን እነዚህ ድርግቶቸ ከየትኛዉ የሙስና ወንጀል ስር ይመደባሉ?

## 1.9. የማጠቃለያ ጥያቄዎች

ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች አመቻቹ በሚያደራጁት ቡድን መሰረት ተወያይታችሁ የደረሳችሁበትን ለተሳታፊዎች አቅርቡ፡፡

1. “ያለአግባብ ጉዳይን ማጓተት” በዘርፋችሁ እንዴት እንደሚስተዋሉ፤ የሚያስከትሉትን ጉዳት ተወያይታችሁ ለተሳታፊዎች አቅርቡ፤
2. በዘርፉ ተዘወትረው የሚታዩት የሙስና ወንጀል ዓይነቶች የትኞቹ ናቸው? ምክንያታችሁን አስረዱ፡፡

3. “ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ ወንጀል” ን ለመከላከል የሃብት ምዝገባ እንዴት ሊከላከል እንደሚችል አስረዱ፡፡

## 1.10. ማጠቃለያ

በዚህ ምእራፍ ውስጥ ሙስና ለሚለው ጽንሰ ሃሳብ አንድ ወጥ የሆነ ዓለም አቀፋዊ ብያኔ መስጠት እንደማይቻል ተመልክተናል፡፡ በተጨማሪም የሙስና ወንጀል መገለጫ ጉቦ ብቻ እንዳልሆም መገንዘብ ተችሏል፡፡

በዚህ ንኡስ ክፍል ስለሙስና ወንጀሎች ታሪካዊ እድገት ማለትም ከ1949 የወንጀሀኛ መቅጫ ህግ ጀምሮ እስከ አዋጅ ቁ. 881/2007 ያለውን ታሪክ በአጭሩ ለማቅረብ ተሞክሮአል፡፡ በዚህ መሰረትም በ1949 በወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ህግ፣በ1967 በወጣው አዋጅ ቁጥር 8/1967 እንዲሁም የዚሁ ማሻሻያ ሆኖ በወጣው አዋጅ ቁጥር 214/1974 ልዩ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ሙስና ተብሎ ባይታወቅም ነገር ግን ስልጣንን አለአግባብ መገልገልን የሚመለከቱ የወንጀል ድንጋጌዎች የነበሩ ስለመሆኑ ቀርቧል፡፡

ሙስና የሚለው ቃል ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ህግ ስርአት የገባው በ1993 በወጡት የጸረ ሙስና ህጎች (የጸረ ሙስና ልዩ ስርአትና የማስረጃ ህግ ቁ. 236/93) እንደሆነ እና ከዚህ ቀጥሎ የሙስና ወንጀል ህጎች እየተሻሻለ አሁን በስራ ሊይ ያለው የሙስና ወንጀል አዋጅ ቁ.881/2007 ድረስ ያለው የሙስና ወንጀሎች የህግ እድገት ታሪክ በአጭሩ ቀርቧል፡፡ በመቀጠልም በአዋጁ የሙስና ወንጀል ምንነትን የሚገልጸው ‹መርህ› ያካተታቸው መሰረታዊ ሀሳቦች እንዱሁም የሙስና ወንጀል በመንግስት ሰራተኛ፣ በህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ እንዲሁም በማንኛውም ሰው የሚፈጸም ስለመሆኑ ተብራርቷል፡፡ከዚህ አኳያ በአዋጅ ቁጥር 881/2007 የተደነገጉትን 25 የሙስና ወንጀሎችን ለማየት ተችሏል፡፡ በዚህ ምእራፍ ውስጥ የቀረቡት የሙስና ወንጀሎች ትርጓሜ ናቸው፡፡ የወንጀሎቹን ዝርዝር ጉዳይና የሚጣለውን መቀጮ በተመለከተ አዋጅ ቁጥር 881/2007ን ተጨማሪ ንባብ እንዲያደርጉ ይጠበቃል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# የኢንዱስትሪ ዘርፍ ለሙስና ያለው ተጋላጭነትና ዘርፉን የሚመለከቱ ብልሹ አሰራሮች

## 2.1. መግቢያ

ከዘርፍ ተኮር የሙስና መከላከያ ስልቶች አንዱ የሙስና ተጋላጭነት ስጋትን መለየት ነው፡፡ ተቋማት የአሰራር ስርዓት ቢዘረጉም፣ በየጊዘው ደንብና መመሪያ የሚያሻሽሉ ቢሆንም ሙስና እና ብልሹ አሰራርን ከመከላከል አንጻር እዚህ ግባ  የሚባል ለውጥ ማምጣት አልቻሉም፡፡ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣ የኢትየጵያ ኢንተርፕርይዝ ልማት እና የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩትም ከዚህ የተለይ አይደለም፡፡ ስለሆነም ሙስናን ለመከላከል በሚደረገው ጥረት የኢንዱስትሪ ዘርፍና ተጠሪ ተቋማትን ለሙስና የሚያጋልጡ ጉዳዮችን መለየት አስፈላጊና ወሳኝ ነው፡፡ እነዚህ የኢንዱስትሪ ዘርፉን ለሙስና ተጋላጭ የሚያደርጉ ሁነቶች ወደ ሙስና ከመሸጋገራቸው በፊት ዕርምጃ መውሰድ ስለሚገባ ከወዲሁ መለየት ሙስናን ለመከላከል በሚደረገው ጥረት ወሳኝ ሚና አለዉ፡፡

ከተጋላጭነት በተጨማሪ በዚህ ክፈል ዉስጥ በኢንዱስትሪ ዘርፍ የሚከሰቱ የሙስናና ልዩ ልዩ የብልሹ አሰራሮችም ቀርበዋል፡፡ በአገሪቱ የልማትና  የኢኮኖሚ እድገት ላይ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ካላቸው ተቋማት መካከል አንዱ የሆነው  ኢንዱስትሪ ዘርፍ ከሚያከናውኗቸው  ዘርፈ ብዙ እና ውስብስብ ስራዎች አንጻር  ለሙስና እና ብልሹ አሰራር የመጋለጥ እድሉ ሰፊ ነዉ፡፡ ዘርፉ በልማትና ኢኮኖሚ ዘርፍ የሚጫወተው ሚና የላቀ መሆኑ፤ ለአገሪቱ ዕድገት መሠረት ከመሆኑም በላይ ከተለያዩ ተቋማት ጋር ያለው ትስስር ከፍተኛ መሆኑ ዘርፉ ለሙስና ችግሮች የተጋለጠ እንዲሆን አድርጎታል፡፡

## 2.2. የምዕራፉ ዓላማ

ሰልጣኞች  ከዚህ ምዕራፍ ስልጠና በኋላ፡-

1. የኢንዱስትሪ ዘርፉን የሙስና ተጋላጭነት ያብራራሉ፡፡
2. የኢንዱስትሪ ዘርፉን ለሙስና የሚያጋልጡ ሁኔታዎችን ይለያሉ፡፡

3. አመራሮች ለምን የሥነ ምግባርና የሠራተኛ ክፍልን በበጎ እይታ እንደማይመለከቱት ይጠቁማሉ፡፡
4. በኢንዱስትሪ ዘርፍ የሚከሰቱ ሙስናዎችን ይለያሉ፡፡
5. የሙስና ተግባር ምን ያህል ውስብስብ እንደሆነ ያብራራሉ፡፡
6. የቀረቡትን የሙስና ምሳሌዎች የሙስና በሮችን ለመዝጋት እንደማነቃቂያ ደዉል ይጠቀሙባችዋል፡፡

### 2.3. የተመደበው ጊዜ

ይህን ምዕራፍ ለማጠናቀቅ የተመደበው ጊዜ 8:00 ሰዓት

### 2.4. የማነቃቂያ ጥያቄዎች

<u>ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች በቡድን ተወያዩበትና የደረሳችሁበትን ላተሳታፊዎቸ አቅርቡ፡፡</u>

1. ለሙስና መንስዔ የሆኑና ሊሆኑ የሚችሉ ሁነቶች ምንድናቸዉ?
2. ለሙስና መነሻ የሆኑ ሁነቶች ምንጫቸዉ ዉስጣዊ ወይም ዉጫዊ ነዉ? አብራሩ፡፡
3. በኢንዱስትሪ ዘርፍ ዉስጥ ስለመከሰቱ የሚታዉቁትን አንድ የሙስና ድርጊት ከግማሽ ነጭ ወረቀት ባላነስ ከሙሉ ነጭ ወረቀት ባልበለጠ መጠን ጽፋችሁ ለአሰልጣኙ አስረክቡ፡፡ አስልጣኞች ከነዚህ መሀል ጠቃሚ ናቸዉ ብለዉ ያሰቡትን በመምረጥ ለመማማሪያነት ያቅርቡ፡፡

### 2.5. የዘርፉ ለሙስና ተጋላጭነት

በ2015 ዓ/ም በጸረመስና ኮምሽን የተደረገ ጥናት እንደሚያሳየዉ የእንዱስትሪ ሚኒስቴር የስነምግባር ክፍሉን በሰው ሃይል ለማሟላት ያደረገው ጥረት ጥሩ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ክፍሉ የበጀት ነፃነት ያለው አይመስልም፡፡ ለክፍሉ ተብሎ የተመደበ በጀት አለመኖሩ ስራዎች በተቋም አመራር ውሳኔና ፍላጎት ላይ የተመሰረቱ ያደርጋቸዋል፡፡ አመራሩ ስራውን ከግል ፍላጎቱ በመነሳት ሲያምንበት በጀት የመፍቀድ ሁኔታ ሊኖር ስለሚችል ክፍሉ ስራውን ያለጣልቃ ገብነት ሊሰራ መቻሉ አጠራጣሪ ነው፡፡ የስነምግባርና የጸረሙስና ክፍልን መስሪያ ቤቶች ብዙን ጊዜ በበጎ

አይን አይመለከቱትም። በሞጁሉ ጸሐፊዎች በተደረገው ጥቂት ዳሰሳ የየትኛዉም መስሪያ ቤት ህላፊ የስነምግባርና የጸረሙስና ክፍል የማስተዳድረዉን ተቀዋም ከሙስናና ብልሹ አሰራር የጸዳ እንዲሆን ይረዳኛል ከማለት ይልቅ ብዙን ጊዜ ክፍሉን እንደ ባላንጣና አሳጭ መመልከት አንዲሁም መፍራት ይታያል። በመሆኑም ለክፍሉ አስፈላጊዉን በጀት በመመደብ ስራዉን በአግባቡ እንድውጣ ያለማድረግ መስሪያ ቤቶችን ለሙስናና ብልሹ አሰራር ተጋላጭ ያደርገዋል።

በተጨማሪም ኢንዱስትሪ ዘርፍ ስር የሚገኙ ሁሉም ተቋማት የሰነድ ሪፖርቶች ማየት እንደተቻለው የሥነ-ምግባር እና ፀረ-ሙስና ክፍል የስራ አፈጻጸም ግምገማ ሙስና አሁን ካለበት አስጊ ገጽታ አንጻር ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት ክፍሉ ለብቻው በበላይ ሃላፊዎች የሚገመገምበት የአሰራር ስርዓት አለመኖሩን በጥናቱ ለማወቅ ተችሏል።

### 2.5.1. ከኤክስፖርት ማበረታቻ እና ድጋፍ ጋር የተያያዘ

- አለም ዓቀፍ ማህበራዊና ከባባዊ አስገዳጅ መስፈርቶችን ያላሟሉ ምርቶች ሲመረቱ አግባብነት የሌለዉ ጥቅም ለማግኘት በቸልታ ማለፍ፣
- በተደረገላቸዉ ኤክስፖርት ማበረታቻ መሠረት ወደ ዉጭ ገበያ መግባት ሲገባቸዉ ባለመግባት መንግስት ማግኘት ያለበትን ጥቅም ማሳጣት
- በክትትልና ድጋፍ ስም የራስን ጥቅም በማስቀደም ዋናና መደበኛ የሆነዉን የድጋፍና ክትትል ስራ በአግባቡ ሳይሰሩ መቅረት፣
- የወጪ ምርቶች ልማትን ለማፋጠን የሚረዱ ፕሮጀክቶችን ለታለመላቸዉ ዓላማ በአግባቡ አለማዋልና አፈጻጸማቸውን ግልጽና ተጨባጭ በሆነ ሁኔታ አለመገምገም፣
- የሚሰጡ የኤክስፖርት ማበረታቻ ድጋፎች ከዓላማ ዉጪ ስራ ላይ ማዋል
- የኮንትሮባንድ እና ህገወጥ ንግድ መስፋፋት

### 2.5.2. የፍቃድ አሰጣጥ እና እድሳት

- በሀገር ዉስጥ ባለሙያዎች የሚሸፈኑ የስራ መስኮች ላይ ያልተገባ ጥቅም በማሰብ ለዉጭ ባለሙያዎች አዲስ የስራ ፍቃድ እና እድሳት መስጠት

- የኢንዱስትሪ ባለቤቶች እና ከዉጭ በሚመጡ ባለሙያዎች በተስማሙበት የክፍያ ስርዓት መሠረት አለመፈፀም
- በዘርፉ ለሀገር ዉስጥ የሙያ ፍቃዶች ህግና መመሪያን መሠረት ሳያደርግ መስጠት

### 2.5.3. <u>የብቃትና ፈቃድ አገልግሎት አሰጣጥ</u>

- ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ እና ሀገር ውስጥ የሚመረቱ የኢንዱስትሪ ኬሚካሎች ለአደጋ አጋላጭነታቸው ደረጃ፣ የአገልግሎት ጊዜያቸውን፣ እንዲሁም በኬሚካል ባህሪያቸው መነሻ ያደረጉ የአወጋገድ ስርዓታቸውንና መሰል ክፍተቶችን በጥናት እንዲለዩና እንዲታወቁ ከማድረግ ይልቅ ከባለሀብቱ ጋር በመደራደር ሽፋፍኖ ማለፍ፣
- ጥብቅ የአጠቃቀም ገደብ የተጣለባቸውን የኢንዱስትሪ ኬሚካሎችን ወደ ሀገር ውስጥ ሲገቡና ወደ ውጪ ሲወጡ፤ የኬሚካሉ ምዝገባ ቁጥር፣ መጠሪያ ስም፣ መጠን፣ የአገልግሎት አይነት፣ የተመረተበትና የአገልግሎት ማብቂያ ጊዜ እንዲሁም የኬሚካሉ ባህሪና የንጥረ ነገር ይዘት የሚያሳይ መረጃን መሰረት ያላደረገ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት በድርድር እንዲያገኙ ማድረግ
- የዘርፍ ሙያ ማህበራት ተገቢዉን መስፈርት ሳያሟሉ በመደራደር ያልተገባ ፍቃድ መስጠት

### 2.5.4. የማማከር፣ የጥናት እና ምርምር ስራ

- በማይተገበር የጥናት እና ምርምር ርእስ ላይ በጀት አስይዞ ያልተገባ ጥቅም ማግኘት
- በሌላ ሰዉ እና በቡድን የተጠኑ ጥናቶችን በአቋራጭ ጥቅም ለማግኘት የራስ አስመስሎ ማቅረብ
- በዘርፉ በጀት አማካኝነት የተሰሩ የጥናት እና ምርምር ዉጤቶችን ባልተገባ የጥቅም ትስስር ምክንያት ለሌላ አካል አሳልፎ መስጠት
- ከዘርፉ እዉቅና ዉጭ በጥናት እና ምርምር ስራ ስም ያልተገባ ጥቅም በመሻት ከአምራች ኢንዱስትሪዉ ጋር መመሳጠር/መደራደር
- የማማከር፣ የጥናት እና ምርምር ስራዎችን በጥብቅ ዲሲፕሊን እና ሙያዊ ስነምግባር ተከትሎ አለመስራት

### 2.5.5. መንግስት ለባለሀብቶች ከሚሰጣቸዉ የማበረታቻ እና ማስፋፍያ እንዲሁም ግብዓት ድጋፍ ጋር የተያያዘ

- ከቀረጥ ነፃ የሚገቡ ምርቶች ለታለመላቸው ዓላማ እንዳይውሉ በሚደረግበት ወቅት እንዳላዩ በማለፍ ከዘርፉ ጋር በመደራደር ጥቅም ማጋበስ፣
- በየዘርፎቹና ምርቶች ላይ የግብዓት ጥምርታ መሠረት ከማድረግ ይልቅ ተጠቃሚዎች የሚያሳውቁትን ተቀብሎ ማፅደቅና ከሚገኘው ጥቅም ተጋሪ መሆን፣
- የግብዓት ምርት ጥምርታን መሠረት ያላደረገ ግብዓት በመጠየቅ ያልተገባ ጥቅምን መፈለግ
- የታክስ ማበረታቻ ስርዓትን ላለተፈለገ ዓላማ እንዲውል ማድረግና በምትኩ ከሚገኘው ጥቅም ለመጋራት መሞከር፣
- በስራ ላይ ያሉ ህጎች በትክክል ስራ ላይ እንዳይውል ማድረግና በሚፈጠረው ችግር ጥቅም መሻት፣

### 2.5.6. ኢንተርፕራይዞችን ከመደገፍና ማልማት ጋር የተያያዘ

- ወደ ኢምፖርየም በሚገቡ ምርቶች በርክክብ ወቅት በጥቅም ግንኙነት የሚፈጸም ደረጃውን ያልጠበቀ ምርት መረከብና በሽያጭ ሂደቱም ለመንግስት መግባት ያለበትን ገቢ አለመሰብሰብ፣
- በኤግዚብሽን ላይ የሚሳተፉ የኢንዱስትሪ ባለቤቶችን በተደጋጋሚነት በጥቅም ላይ በተመሰረተ ሁኔታ እንዲሳተፉ ማድረግ
- በኢምፖሪየም የሚጠቀሙ አምራች ኢንዱስትሪ ባለቤቶች የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ሲያበቃ ወቅቱን ጠብቀው ለተተኪው የኢንዱስትሪ ባለቤት እንዲለቁ ያለማድረግ፣
- ከአነስተኛ ወደ መካከለኛ የሚደረግ የደረጃ እድገት ሽግግር ህግና መመሪያን ተከትሎ ከመስራት ይልቅ የአምራቹን ፍላጎት መሠረት በማድርግ የግል ጥቅምን ማስቀደም
- ለኢንተርፕራይዞች የሚሰጠዉ ብድር እና የሊዝ ፋይናንስ አገልግሎት አሰጣጥ የግለሰብ ጥቅምን መሠረት በማድረግ አገልግሎት መስጠት

### 2.5.7. የአላቂ እና ቋሚ እቃዎች እንዲሁም የአገልግሎት ግዥ ጋር የተያያዘ

- ከማዕቀፍ ግዥ አንፃር በጥራት የተመረጠው ዕቃ ተመሳሳይ በሆነ ጥራቱን ባልጠበቀ ዕቃ ተተክቶ መቅረብ፣
- በዋጋ ማቅረቢያ ወይም ፕሮፎርማ ከሚፈጸም ግዥ አንፃር በተወሰነ አካባቢ ከሚገኙ አቅራቢ ድርጅቶች በተደጋጋሚ የዋጋ ማቅረቢያ ማቅረብ፣
- ከውስን ጨረታ አንፃር አቅራቢው የሚመረጥበት የምርጫ ሂደት ለአድልኦ እና ወገንተኝነት የተጋለጠ መሆኑ፣
- ከጨረታ ሰነድ ዝግጅት የጨረታ ኮሚቴ ትንተና እና የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት አንፃር የጨረታ ውጤት ገለፃ እና የቅሬታ አቀራርብ ስርዓት ላይ የሚታይ የግልፅነት መ[1]ደል መኖሩ፣

### 2.5.8. መሠረታዊ የአገልግሎት እና ንብረት አስተዳደር

- የክፍያ ትዕዛዝ የሚቀርብባቸው የእቃና የአገልግሎት ክፍያዎች በመመሪያው መሰረት መሟላት የሚገባቸውን ሰነዶች ሳያሟሉ ክፍያ መፈፀም፣
- በጥቅል ግዥ አቅራቢዎች የሚያቀርቡት ዋጋ ከገበያዉ የዋጋ አቅርቦት ጋር ሲነፃፀር ከፍተኛ መሆኑና የገበያ ጥናት አለማድረግ
- ያልተገባ ጥቅምን ታሳቢ በማድረግ የቴክኒካል እና የፋይናንሻል እስቴስፊኬሽን መሠረት ያላደረገ የዕቃ ርክክብ ማድረግ
- የንብረት አቅርቦት፣ ስርጭት፣ አጠቃቀም እና ማስወገድ አሰራር ላይ ክፍተት መኖር፣
- ጥቅም ላይ የሚውሉ እና የማይውሉ ንብረቶች አለመለየታቸውና ተጨማሪ ግዥ እንዲፈፀም ማድረጉ፣
- ተገዝተው የሚገቡ እቃዎች በተዘጋጀው ስፔስፊኬሽን መሆኑን አረጋግጦ ገቢ አለማድረግ፣
- ተገዝተው የሚቀርቡ ዕቃዎችን በወቅቱ ለሚመለከተው ስራ ክፍል በዕቅዱ መሰረት ወጪ እንዲደረግ አለማድረግ፣
- ከተሽከሪካሪዎች ስምሪት ጋር በተያያዘ የተገልጋዮች አለመርካት፣
- ከስራ ሰዓት ዉጪ ተሽከርካሪ በህገ ወጥ መንገድ ለግል ስራ ጥቅም ላይ ማዋል

- ከተሽከርካሪዎች እድሳት፣ ነዳጅ እና ቅባት አጠቃቀም ጋር በተያያዘ ለሙስና በር የሚከፍቱ አሰራር መኖራቸው፣

### 2.5.9. የብቃትና የሰው ሀብት አስተዳደር

- ከቅጥር እና የደረጃ ዕድገት አንፃር የጥቅም ግጭት በሚፈጥር አግባብ መፈፀም፣ የአሰራር ቅደም ተከተሎችን ያልተከተለ የሰራተኛ ቅጥር መፈፀም፣ የስራ መደቡ ከሚጠይቀው የትምህርት አይነት ዝግጅት ውጭ ያለ ሰራተኛ መመደብ፣
- የውጭ አገርና የአገር ውስጥ ስልጠና፤ ልምድ ልውውጥ እና ጉብኝት አንፃር ምልመላ/ምርጫ ግልፅነት መጓደል ቀጥታ ከስልጠናው ጋር አግባብነት የሌላቸው እንዲሳተፉ ማድረግ፣
- በሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃ ቅጥር እና ዕድገት ማግኘት፣
- የሰራተኞችን ፋይል ሚስጥሩን ጠብቆ በአግባቡ አለመያዝ እና አለማስተዳደር

**<u>የመወያያ ጥያቄዎች</u>**

**<u>በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ በቡድን ተወያዩበትና የዉይይቱን ዉጤት ለተሳታፊዎቸ አቅርቡ፡፡</u>**

የሚከተሉት ነጥቦች የኢንዱስትሪ ዘርፉን ለሙስና የሚያጋልጡ ተብለዉ የተለዩ ሲሆኑ ነጥቦቹ በትክክል ስለመከሰታቸዉ የራሳችሁን ምልከታ ስጡና እንዴት ተቋማቱን ለሙስና ተጋላጭ እንዳደረጓቸዉና እንደሚያደርጓቸዉ በምሳሌ አብራሩ፡፡

- የጥቆማ መቀበያ ስርአት ቢኖርም በጥቆማዎች ላይ ተመስርቶ የተወሰደ እርምጃ ስለመኖሩ የሚየያሳይ መረጃ አለመገኘቱ፤
- የህግ ክፈሎች በሚፈለገው አቅም የደረጁ አለመሆናቸው፡፡
- ከሶስቱ ተቅዋም በሁለቱ ካይዘን ተግባራዊ አለመደረጉና የሙስና ስጋት ስርዓት ጥናት ስለመደረጋቸዉ የሚያሳይ መረጃ አለመገኘቱ፤
- የአምራች ዘርፉ መረጃን በተደራጀ መልኩ በአግባብ አለመያዝ፣ ግልጽነትና ተጠያቂነት አለመኖር፣
- ለአሰራር የሚረዱ የህግ ማዕቀፎች፣ መመሪያዎችና ደንቦች ወዘተ በተደራጀ ሁኔታ በአግባቡ ስራ ላይ አለመዋላቸዉ.
- በጸረ ሙስና ትግሉ ላይ የአመለካከትና የተነሳሽነት ደረጃ እኩል ተሳትፎ አለመኖሩ፣

- የአንዳንድ የስራ ክፍሎች ስራ በደንቦችና መመሪያዎች አለመደገፌቸው ስራዎችን በታለመውና በተፈለገው አግባብ አለመስራት፣
- ልማዳዊ አስተሳሰቦችና አሠራሮች መኖራቸው፣
- ግዥን በዕቅድ አለመምራት፣
- የስነምግባር ክፍሉ ከሌሎች የተቋሙ አደረጃጀቶች ጋር በቅንጅት የሚሰራበት መደበኛ አሰራር አለመኖሩ፤

## 2.6. በዘርፍ የሚስተዋሉ ሙስና እና ብልሹ አሰራሮች

በኢንዱስትሪና ዘርፍ አውድ ውስጥ ያለው ሙስና ራሱን በተለያዩ መንገዶች ሊገለጽ ይችላል። ኢንዱስትሪ ዘርፍ ከሚያከናውኗቸው ዘርፈ ብዙ እና ውስብስብ ስራዎች አንጻርና ከተለያዩ ተቋማት ጋር ያለው ትስስር ለሙስና እና ብልሹ አሰራር የመጋለጥ እድሉን አስፍቶታል። በኢንዱስቲሪ ሚኒስቴር (2016 ዓ/ም) የኢንዱስትሪ ዘርፍ የሙስና መከላከያ ስትራቴጂክ እቅድ (ከ2017 እስከ 2023) የኢንዱስትሪ ዘርፍ የሙስና ሥጋት ግምገማዊ ጥናት በሚል ጥናት ላይ እንደተመከተዉ የሚከተሉት ሙስና እና ብልሹ አሰራሮች በኢንዱስትሪ ዘርፍ ተከስተዋል። እነሱም፦

### 2.6.1. ጉቦ መስጠትና መቀበል

ጉቦ በመስጠትና በመቀበል ስር የተከሰቱ የሙሰና ተግባሮች፦

- የማምረቻ ተቋማት ለባለስልጣናት ጉቦ መስጠትና ይህን ተጠቅሞ የኢኮኖሚ ማዕቀቦችንና የኤክስፖርት ቁጥጥርን መጣስ እና ግብር መሰወር።
- የሀገር ውስጥ ባለስልጣናትን በጉቦ በመደለል በኢንዱስትሪ የሚመጣን የማሕበረሰብ ብዝበዛና የአካባቢ መራቆትን መሸፋፈን።
- ድርጅቶች ህጋዊ ደረጃዎችን ሳያሟሉ ሲቀሩ ከደንቦች (REGULATION)፣ ክትትሎች (FOLLOW UPS) ፤ ፍተሻዎችና (INSPECTION) ቁጥጥሮች (SUPERVISSION) ለማምለጥ ጉቦ መስጠት። በመሆኑም ለአካባቢውና ለህብረተሰቡ ደህንነት ተስማሚነታቸው የተረጋገጡ መሆናቸውን ሳያጣሩ በማህበረሰቡ ደህንነት ላይ ያለአግባብ መደራደር ወይም በቸልታ ማለፍ።

- ለኢንተርፕራይዞች የሚሰጠዉ ብድር እና የሊዝ ፋይናንስ አገልግሎት እና ከአነስተኛ ወደ መካከለኛ የሚደረግ የደረጃ እድገት ሽግግር ህግና መመሪያን ሳይከተሉ በጥቅም መስራት፡፡

### 2.6.2. ያለአግባብ ፍቃድ መስጠት ወይም ማፅደቅ

ያለአግባብ ፍቃድ መስጠት ወይም ማፅደቅ ስር የተከሰቱ የሙሰና ተግባሮች፦

- ኩባንያዎች ብቃት ሳይኖራቸዉ ኮንትራት ለማግኘት ለመንግስት ባለስልጣናት ጉቦ በመስጠት ጫራታዎችን ማሸነፍ፡፡ ይህ ደግሞ ደረጃውን ያልጠበቀ ማሽን፤ ዉጤታማና ቀልጣፋ ያልሆን ሥራ፣ የዋጋ ጭማሪ፤ የሰዉ ሕይውት መጥፋትና አካል ጉለት፤ የአክባቢ ብክለትና፤ የሃብት ብክነትን እያስከተለ ይገኛል፡፡

### 2.6.3. ሥልጣን ያለአግባብ መገልገል

ሥልጣን ያለአግባብ መገልገል ስር የተከሰቱ የሙሰና ተግባሮች፦

- በዘርፉ ውስጥ ያሉትን የሕግ ማዕቀፍና የአሠራር ክፍተቶችን በመጠቀም ግልጽነትና ተጠያቂነት የሌለ የነዳጅ ፍጆታና የአደረጃጀት ችግር መፈጸም፡፡
- የአሰራር ቅደም ተከተሎችን ያልተከተለ የሰራተኛ ቅጥር መፈፀም፣ የስራ መደቡ ከሚጠይቀው የትምህርት አይነት ዝግጅት ውጭ ያለ ሰራተኛ መመደብ፣ ሰራተኛን ከአሰራር ዉጭ በሆነ አካሔድ ከደረጃ ማዉረድና ከስራ ማሰናበት፡፡
- ከውስን ጨረታ አንፃር አቅራቢው የሚመረጥበት የምርጫ ሂደት ለአድልኦ እና ወገንተኝነት የተጋለጠ መሆኑ፣

### 2.6.4. ያለአግባብ ጉዳይን ማጓተት

ያለአግባብ ጉዳይን ማጓተት ስር የተከሰቱ የሙሰና ተግባሮች፦

- ለኢንዱስትሪያሊስቶ የሚመቻች መሠረተ ልማቶች፣ የመሬት ጥያቄዎች በጊዜ አለማመቻቸት እና እጅ መንሻ መጠየቅ፡፡

- ከጨረታ ሰነድ ዝግጅት የጨረታ ኮሚቴ ትንተና እና የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት አንፃር የጨረታ ውጤት ገለፃ እና የቅሬታ አቀራርብ ስርዓት ላይ የሚታይ የግልፅነት ችግር፡፡
- በኢምፖሪየም የሚጠቀሙ አምራች ኢንዱስትሪ ባለቤቶች የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ሲያበቃ ወቅቱን ጠብቀው ለተተኪው የኢንዱስትሪ ባለቤት እንዲለቁ ያለማድረግ፡፡

<u>ኬዝ አንድ</u>

"JKA" የሚባል የቆዳ አምረች ድርጅት ፋብሪካውን አቋቁሞ ምርት ወደ ማምረት ገባ፡፡ ይሁን እንጂ የአከባቢው ማህበረሰብ ከፋብሪካው የሚወጡ ቆሻሻዎች እና ተረፈ ምርቶች አከባቢውን እየበከሉ ስለሆነ መፍትሔ እንዲሰጣቸው በተደጋጋሚ የፋብሪካውን ሥራ አስኪያጅ ሲጠይቁ ቆይተዋል፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ ባለሀብቱ አንድ ከራሱ ጋር ቅርበት ያለውን ከፍተኛ አመራር በመጋበዝ ፋብሪካውን እንዲጎበኝ ያደርጋል፡፡ ፋብሪካዉም የተለምደዉ ብክለቱነ በነጻነት ይቀጥላል፡፡ በጉብኝቱም ቀን የአከባቢው ማህበረሰብ ግልብጥ ብሎ ወጥቶ ለአመራሩ አቤቱታውን ያቀርባል፤ ነገር ግን ምላሽ ጠፋ፡፡ በዚህም ሳያበቃ ማህበረሰቡ ተወካዮችን መርጦ ወደ "ZKA" የልማት ድርጅቶች አስተባባሪ መሥሪያ ቤት በመሄድ አቤቱታውን በማመልከቻ እና በአካል ያስረዳል፡፡ ሆኖም ግን አዉንታዊ ምላሽ ስላልተገኘ የአካባቢዉ ማሕበረሰብ ልማት ድርጅቱን ምርት ወደ ማስቆም ይሸጋገራሉ፡፡

***የመወያያ ጥያቄዎች***

<u>በቀረበዉ ኬዝ ላይ በመመስረት የሚከተሉትነ ጥያቄዎቸ በተናጠል ስሩና ዉጤቱን ለተሳታፊዎች አቅርቡ፡፡</u>

1. በኬዙ ምን ምን የሙስና ድርጊቶች ታይተዋል?
2. የ"ZKA ዳይሬክተር ብትሆኑ ምን ታደርጋላችሁ?
3. የ"ZKA የህብረተሰብ ጤና ክትትልና ቁጥጥር ባለሙያ ብትሆኑ ምን ታደርጋላችሁ?
4. የ"ZKA የአከባቢ ቁጥጥር እና ክትትል ባለሙያ ብትሆኑ ምን ታደርጋላችሁ?
5. የሥነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ክትትል ዳይሬክተር ብትሆኑ ምን ታደርጋላችሁ?

## <u>ኬዝ ሁለት</u>

አንድ “የኛ” የተባለ የእንጀራ አቅራቢ ኢንተርፕራይዝ አራት አባላትን ይዞ በህጋዊ መንገድ ተደራጅቶ ወደ ሥራ ከገባ እነሆ 13 ዓመታት ተቆጥረዋል፡፡ ይህ ኢንተርፕራይዝ በተደራጀ በአንድ ዓመት ውስጥ የእንጀራ መጋገሪያ ሼድ (12 በ 20 ሜ የሆነ ቤት) ለመሥርያነት ይሰጠዋል፡፡ የኢንተርፕራይዙ ሥራ አስኪያጅ ከክ/ከተማው የኢንተፕራይዞች ማምረቻ ማዕከላት አስተዳደር ኃላፊዎች ከአንዱ ጋር የሥጋ ዝምድና እንዳለው ይነገር ነበር፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ የሼዱን ኪራይ አይከፍልም፤በተጨማሪም ከሌላ ክ/ከተማ ተመሣሣይ ሼድ ወስዶ እየሠራ መሆኑ ጥቆማ ላደራጀዉ ወረዳ ማዕከላት አስተዳዳሪ ባለሙያ ለአቶ ባልቻ ይደርሰዋል፡፡ የኢንተርፕራይዙ የዕድገት ደረጃ ሽግግር ሰርተፊኬት በሚታይበት ጊዜ ጀማሪ ይላል፤ሰርተፊኬቱ የተፈረመው አቶ ጉርሙ ተብሎ በሚጠራው የአደራጅ ወረዳ የእድገት ደረጃ ባለሙያ ነው፡፡

**የመወያያ ጥያቄዎች**

<u>የሚከተሉትን ጥያቄዎች  በኬዙ መሠረት በቡድን ተወያዩበት፡፡</u>

1. በዚህ ኬዝ የተከሰቱ የሙስና ድርጊቶች ምን ምን ናቸው?
2. አቶ ባልቻን ብትሆኑ ምን ታደርጋላችሁ?
3. አቶ ጉርሙን ብትሆኑ ምን ታደርጋላችሁ?

### 2.7. የማጠቃለያ ጥያቄዎች

<u>የኢንዱስትሪ ዘርፍ ለሙስና ያለው ተጋላጭነትና የሚከሰቱ ሙሰናዎች ላይ ስልጠና ከወሰዳችሁ በኋላ የሚከተሉትን ጥያቄዎቸ በቡድን ሰርታችሁ አብራሩ፡፡</u>

1. የኢንዱስትሪ ዘርፍን ለሙስና ተጋላጭ የሚያደርጓቸዉን ሌሎች ያልተነሱ ነጥቦች ጥቀሱ፡፡
2. የኢንዱስትሪ ዘርፍ ለሙስና ያላቸዉን ተጋላጭነት ለማስወገድ የሚረዱ የመፍትሄ ሃሳቦች ምንድናቸዉ?
3. የተቋማት አመራሮች ለምን የሥነ ምግባርና የጸረ ሙስና ክፍልን በበጎ እይታ እንደማይመለከቱ አብራሩ፡፡

4. በስልጠናዉ ላይ የተመለከቷቸቸዉ በኢንዱስትሪ  ዘርፍ የታዩ የሙስና ድርጊቶችን እንዴት ትገመግሟቸዋላችሁ?
5. በስልጠናዉ ላይ የተመለከቷቸቸዉ በኢንዱስትሪ ዘርፍ የታዩ የሙስና አይነቶችን ሙስና ነዉ ብላችሁ አስባችሁ ታውቃላችሁ? ያብራሩ።

### 2.8. ማጠቃለያ

የሙስና ተጋላጭነት ተቅዋምን ከራሱ የስራ አፈጻጸምና አከዋወን የተናሳ ለሙስናና ብልሹ አሰራር የሚያጋልጡት ሁነቶችን የሚያመላክት ነው። የተቋሙን የአሰረር ስርዓት አደጋ ላይ የሚጥል፣ ለሙሰናና ብልሹ አሰራር የሚያጋልጥ እና ማህበረሰቡ በተቋሙ ላይ ያለውን አመኔታ የሚያሣጣ በተደጋጋሚ በሚከሰት ብልሹ አሰራር ድግግሞሽና እና ብልሹ አሰራሩ ቢከሰት ሊፈጥር በሚችለው ተፅዕኖ ምክንያት የሚለካ ነው። በመሆኑም በኢንዱስትሪ ዘርፍ ባለው የስራ ባህሪ፣ ከሚንቀሳቀሰው ሃብትና ካለው የአስራር ስርዓት አንፃር የፌደራል የስነ ምግባርና ጸረ ሙስና ኮሚሽን (2015 ዓ/ም) በኢንዱስትሪ ዘርፍ የሙስና ሥጋት ግምገማዊ ጥናት በሚለዉ ሞጁል ላይ የሙስና ተጋላጭነትን በደረጃ አስቀምጧል። በዚህ መሰረት የግዥ አገልግሎት ከፍተኛ፣ የንብረት አስተዳደር መካከለኛ፣ ተሽከርከሪን በተመለከተ (ስምሪት፣ነዳጅ አጠቃቀምና ጥገና) መካከለኛ፣ የፋይናንስ አገልግሎት መካከለኛ፣ የሰዉ ሀብት ልማት መካከለኛ፣ የገበያ ልማትና የኢንዱስትሪዎች ትስስር መካከለኛ ተጋላጮች መሆናቸው ተመላክቷል።

በአጠቃላይ በሀገራችን የሚከሰቱ ሙስናዎች ተመሳሳይነት አላቸዉ። የሚፈጸሙትም በተመሳሳይ ጉዳይ ዙሪያ ሲሆን  በኢንዱስትሪ ዘርፍ ዉስጥም እንደሌሎቹ ተቅዋማት የሙስና ችግር ከግዥ፣ ከተሽከርካሪዎች እና ከነዳጅ ግዢና አጠቃቅም ጋር ተያያዥነት አላቸው። በተጨማሪም ኩባንያዎች ብቃት ሳይኖራቸዉ ኮንትራት ለማግኘት ለመንግስት ባለስልጣናት ጉቦ በመስጠት ጫረታዎችን በማሸነፍና ከደረጃ በታች የሆኑትን ፋብሪካዎቸ ማቋቋም ይጠቀሳሉ። በመቀጠልም የሀገር ውስጥ ባለስልጣናትን በጉቦ በመደለል በፋብሪካዎች የሚመጣን የሰዉ ብዝበዛና የአካባቢ መራቆት ጉዳይ ችላ እንዲባል ማድረግ ይጠቀሳል። ከግብዓት ጋር በተያያዘ ከፋብሪካዎች የማምረት አቅም ጋር ያልተመጣጠነ የአቅርቦት ድጋፍ ማድረግ፣ በቡድን የተሰራ ጥናት የግል አስመስሎ፣ ችግር ፈቺ ያልሆነ ጥናት እና ምርምሮችንና ቀደም ብሎ የተሰሩትን ጥናት ከንደገና

ማቅረብ በኢንዱስትሪ ዘርፍ ዉስጥ ታይተዋል ተብለዉ ሪፖርት የተደረጉ የሙሰና ድርጊቶች ናቸው::

# ምዕራፍ ሶስት

## በኢንዱስሪ ዘርፍ የሚስተዋለው ሙስና የሚያስከትለዉ ጉዳትና የመከላከያ ስልቶች

### 3.1. መግቢያ

በኢንዱስትሪ ዘርፍ ያሉ ሙስናዎች ብዙውን ጊዜ ልማትን፣ አስተዳደርን እና ማህበራዊ ደህንነትን የሚጎዱ ናቸዉ። በዋናነት በዘርፉ ያለው የመዋለ ንዋይ ፍሰት እንዲቀንስ በማደረግ በኩል ሙስና ከፍተኛ ሚና አለዉ። የመንግስት ባለስልጣናት ሰራተኞች የተሰጣቸውን የመወሰን ስልጣን በመጠቀም እጅ መንሻ በመቀበል በፍቃድ አሰጣጥ ላይና ገበያ ውድድር ላይ በጎ ያልሆነ ተፅእኖ ያሳድራሉ። ከዚህ በተጓዳኝ ሙስና በአለማቀፍ የሚደረገው የንግድ ውድድርም ላይ አሉታዊ ጥላ ሊያጠላበት እንደሚችል እሙን ነው። ብዙውን ጊዜ ሙስና ለንግድና ኢንቨስትመንት እንቅፋት በመሆን ፍሰቱን ያልተፈለገ ቅርፅ እንዲይዝ የማድረግ አስተዋፅኦ ያለዉ ሲሆን በኢንዱስትሪ ዘርፍ የሚከሰቱ ሙስናዎች የሚያደረሱት ጉዳቶቸ ደግሞ በዚህ ክፍል ዉስጥ ተብራርተዋል።

ስለሆነም በአገራችን ኢኮኖሚ ግዙፍና ዘርፈ ብዙ አስተዋፅኦ ያለው ተቋም በሙስና እና ብልሹ አሰራር ችግሮች ተጋልጦ ግቦቹን እንዳያሳካ ተግዳሮት ከመሆኑ በፊት የተቀናጀ የሙስና መከላከል ስትራቴጂ በመንደፍ ሁነኛ መፍትሔ መሆኑ ታዉቆ ለተግባራዊነቱ ቅድሚያ በመስጠት መንቀሳቀስ ይጠበቃል።

ሙስና ብዙ ዘርፎችን የሚዳስስ፣ መፈጸሚያ መንገዱም በየጊዜው እየተለዋወጠና እየረቀቀ የሚሄድ ወንጀል ነው። ለመከሰቱ ምክንያት የሚሆኑ ጉዳዮችም እንዲሁ በርካታ ናቸው። ታዲያ ይህን ተለዋጭ ባህሪ ያለውን ሙስና ለመዋጋት ዘርፎች እንደየተቋማቸው ባህርይ በየጊዜው የሚሻሻል፣ መጠነ ሰፊ ጉዳዮችን የሚዳስስ የሙስና መከላከልያ ስትራቴጂዎችን መንደፍ ይጠበቅባቸዋል። ሙስናን የመከላከል ተግባር ሙስናና ብልሹ አሰራሮች ሊያስከትሉ የሚችሉትን ከፍተኛ የሆነ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ኪሳራ ለማስቀረት ወይም ለመቀነስ በሚያስችል መልኩ የችግሩን ምንጭ የማድረቅ ተግባር ነው። ሙስናና ብልሹ አሰራርን በመከላከል በሙስናና ብልሹ አሰራር ምክንያት ይባክን የነበረውን ሃብት በመታደግ ያለውን ሃገራዊ ሃብት ለታለመለት ሥራ ለማዋል ያስችላል።

ችግሩ ከተከሰተ በኋላ የችግሩን ፈጣሪ እና የባከነውን ሃብት ለማፈላለግና ለማግኘት የሚባክነውን ተጨማሪ ወጪ ያስቀራል፤ በመንግስት ተቋማት ለሙስናና ብልሹ አሰራር ክፍተት የማይፈጥር ጠንካራ የአሰራር ሥርዓት እንዲፈጠር ያደርጋል፡፡ በዚህ ምእራፍ ውስጥ በዘርፉ ውስጥ ሙስናና ብልሹ አሰራርን መከላከል የሚያስችሉ ስልቶች ይዳሰሳሉ፡፡

### 3.2. የምዕራፉ ዓላማ

ሰልጣኞች ከዚህ ክፍል ስልጠና በኋላ፡-

1. በኢንዱስትሪ ዘርፉ የሚከሰቱ ሙስናዎች በአገሪቱ ኢኮኖሚያዊ፣አከባቢያዊ እና ማህበረሰባዊ እንቅስቃሴዎች ላይ የሚያደርሱትን ጉዳቶች ያብራራሉ፡፡
2. በኢንዱስትሪ ዘርፉ በህብረተሰባችን ላይ የሚደርሱ የተለያዩ ችግሮች በሙስና የተከሰቱ መሆናቸውን ይለያሉ፡፡
3. የሙስና መከላከያ ስልቶችን ይተነትናሉ፣
4. የሙስና መከላከያ ስልቶችን ያወዳድራሉ፣
5. በዘርፉ ውስጥ ያሉ የመከላከለያ ስልቶች ይዘረዝራሉ፣
6. የዘርፋቸውን የሙስና መከላከያ ስልቶች ይገመግማሉ፣
7. በዘርፋቸው የመከላከያ ስልቶችን ይተገብራሉ፣

### 3.3. የተመደበው ጊዜ

<u>ይህን ምእራፍ ለማጠናቀቅ የተመደበው ጊዜ</u> 2:30 ሰዓት

### 3.4. የማነቃቂያ ጥያቄዎች

<u>ከዚህ በታች ያሉትን ጥያቄዎች ከ4 እስከ 5 በመሆን በቡድን ከሰራችሁ በኋላ የደረሳችሁበትን ለተሳታፊዎች አቅርቡ፡፡</u>

1. ከዚህ በታች ባሉት ፎቶዎች ላይ የሚመለከቱት የአካል ጉዳቶች በአንድ የቆዳ ፋብሪካ የተከስቱ ናቸው፡፡ እነዚህ ጉዳቶች በሙስና ምክንያት የደረሱ ስለመሆናቸዉ የሚያስረዳ ፍንጭ አቅርቡ፡፡
2. በኢንዱስትሪ ዘርፍ የሚፈጸም ሙስና የህብረተሰብን መሰረታዊ ፍላጎት መሟላትን እንዴት ሊገታ ይችላል?
3. በኢንዱስትሪ ዘርፍ የሚፈጸሙ ሙስናዎች አገርን እንዴት ሊጎዱ እንደሚችሉ አብራሩ፡፡
4. የምታውቋቸውን የሙስና እና የብልሹ አሰራሮች መከላከያ ስልቶችና ጥቅማቸውን ዘርዝሩ፡፡
5. በዘርፋችሁ ተግባራዊ የሚደረጉ ጠንካራ የሙስና መከላከያ ስልቶች ዘርዝሩ፡፡
6. ሙስናና ብልሹ አሰራርን አስቀድሞ መከላከል የሚያስገኘውን ፋይዳ ምንድናቸዉ? አብራሩ፡፡







ምስል 1፡ በአንድ የቆዳ በኢንዱስትሪ ውስጥ እጃቸው የተቆረጠ ወጣቶች (ፎቶ በፍቃዱ በልዳ፤ ሚያዚያ 9፣ 7 እና 9፣ 2022 በቅደም ተከተል)።

## 3.5. ሙስናና ብልሹ አሰራሮች የሚያስከትሉት ጉዳቶች

### 3.5.1. በተቋም ደህንነት ላይ

ሙስና በማምረቻ ተቋማት ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተፅእኖዎችን እያሳረፈ ይገኛል፡፡

**የመወያያ ጥያቄዎች**

የሚከተሉት ጉዳቶች በኢንዱስትሪ ዘርፍ በሙስናና ብልሹ አሰራሮች ስለመከሰታቸዉ በግል ማብራሪያ ስጡ

- በድርጅቶች አፈፃፀም ላይ አሉታዊ ሚና ማሳደር፡፡
- ጤናማ ያልሆነ የገበያ ውድድር፡፡
- የተቋማት መዳከም፣ የመልካም አስተዳደር ችግርና የውጭ ኢንቨስትመንት መቀነስ፡፡
- ተጎጂዎቸ በኢንዱስትሪዎች ላይ ጉዳት ማድረስ፡፡

**ኬዝ አንድ**

በኢንዱስትሪ ዘርፍ ዉስጥ ወ/ሮ ኪሮስ የምትባል ሰራተኛ በመስሪያ ቤቱ ካሉት ሰራተኞች መካከል በትጋቷ የምትታወቅ ሰራተኛ ነበረች፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ ለአምራቾች የገበያ ትስስር በመፍጠር ላይ የሚሰራዉ አቶ ሀጎስ አላስፈላጊ ጥቅም በመውሰድና የተሰጠን ሃላፊነት በመጠቀም ተመሳሳይ ምርት ከሚያመርቱ አምራቾች ዉስጥ ሁለት ፋብሪካዎች ገቢያ እንዲያገኙ ሲያደርግ ሌሎች አምስት ድርጅቶች ከገበያ እንዲወጡ ያደርጋል፡፡ ይህንን የተመለከተችዉ ወ/ሮ ኪሮስ ድርጊቱን በገሃድ ትቃወማለች፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ ወ/ሮ ኪሮስ በአቅም ማነስ የሐሰት ዉንጀላ ከስራዋ ትባረራልች፡፡

**የመወያያ ጥያቄዎች**

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን በመሆን በጥንቃቄ ሰሩ ዉጤቱን ለተሳታፊዎች አቅርቡ፡፡

1. በዚህ ኬዝ ዉሰጥ በአምራች ድርጂቶች ላይ የተፈጠረውን እክል አብራሩ፡፡
2. በዚህ ኬዝ ዉሰጥ የተፈጠረው የስነ ምግባር ግድፈት ምንድነው?
3. እናንተ ወ/ሮ ኪሮስን ብትሆኑ ምን ታደርጋላችሁ?
4. ወ/ሮ ኪሮስ የሚጠበቅባትን ያህል ሄዳለች ብላችሁ ታምናላችሁ? ያብራሩ፡፡

5. ወ/ሮ ኪሮስ ለአገራቱ ለገባችዉ ቃል ኪዳን ስትል ሥራዋን መስዋዕት ማድረጓ ትክክል ነው ትላላችሁ? አብራሩ።

### 3.5.2. በማህበረሰብ ደህንነት ላይ

ሙስና ሰፊው ህብረተሰብ አየትጎዳ መንግስትና ልሂቃን ሃብትን እንዲመዘብሩ እድል ይፈጥራል። ይህ ድግሞ ወደ ለየለት ግጭት በማምራት ለባሰ ዉድመት ይዳርጋል። ይህ የሃብት መርገምት (RESOURCE CURSE) በመባል ይታወቃል።

- አንዳንድ ኢንዱስትሪዎች ሙስናን ተገን በማድረግ የሠራተኛዉን የሰብዐዊ መብት ጥሰት ይፈጽማሉ። ይህ የጉልበት ብዝበዛ ልማዶችን ያስከትላል።
- ኢንዱስትሪዎች በህገ ወጥ መንገድ ጥሬ እቃ በማምረት ላይ ይሰማራሉ። ይህም አብዛኛውን ጊዜ የሀገር ውስጥ በየደረጃው ያሉትን ባለስልጣናትን በጉቦ በመደለል የአካባቢ መራቆትንና በአክባቢዉ የሚኖሩትን የማህበረሰብ ክፍል ለአደጋና ስጋት ይዳርጋል።
- ኢንዱስትሪዎች ብቃት ሳይኖራቸዉ ኮንትራት ለማግኘት ለመንግስት ባለስልጣናት ጉቦ በመስጠት ጫራታዎችን በማሸነፍ የሚተክሉዋቸዉ ደረጃውን ያልጠበቁ ማሽኖች፤ ዉጤታማና ቀልጣፋ ያልሆነ ሥራ፣ የዋጋ ጭማሪ፤ የሰዉ ሕይውት መጥፋትና አካል መጉደል፤ የአክባቢ ብክለትን፤ የሃብት ብክነትን ያስከትላሉ። ለምሳሌ፣ (ምስል 1ን ተመልከቱ)

### 3.5.3. በአከባቢ ደህንነት ላይ

ኢንዱስትሪ በተለይም የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች በአካባቢ ጥበቃ የተቀመጡ መስፈርቶችን እንዲያሟሉ ድጋፍ ማድርግ ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሥልጣንና ተግባራት አንዱና ዋነኛዉ ሲሆን ሙስና ኢንዱስትሪዎች የአካባቢ ጥበቃን ችላ በማለት አከባቢን ለጉዳት በመዳረግ በተዘዋዋሪ ስዎችን ለጤና፤ ለኢኮኖሚ እያጋለጡ ይገኛሉ።

<u>**ኬዝ ሁለት**</u>

<u>ከዚህ በታች ያሉትን ጥያቄዎች ከጎናችሁ ካለ አንድ ተሳታፉ ጋር በመወያየት ሃሳባችሁን ለሌሎች ተሳታፊዎች አጋሩ።</u>

በምስል 3 እና 4 የሚታዩት ፎቶዎች ኢንዱስትሪዎች ከአከባቢዉ ጋር ያላቸዉን ቁርኝት የሚያሳዩ ናቸዉ፡፡ በምስሎቹ ላይ የሚታዩ ሁነቶች በአከባቢዉ ላይ የሚያደርሱት ጉዳት ያለ ይመስላችኋል? ጉዳቱ በሙስና ምክንያት የደረሰ ስለመሆኑ የሚያስረዳ ፍንጭ ካለ አቅርቡ፡፡







ምስል 3፡ ቆሻሻን በወንዝ ዳር መጣል፣ ማቃጠል እና በህብረተሰቡ መኖሪያ አከባቢ መጣል (ፎቶ በፍቃዱ በልዳ፣ ሚያዚያ 7፣ 7 እና 14, 2022 በቅደም ተከተል)





ምስል 4፡ ከቆዳ ኢንዱስትሪ ወደ ወንዝ የሚፈስ ፍሳሽና የወንዙ ነባራዊ ገጽታ (ፎቶ በፍቃዱ በልዳ፣ ሚያ2022)

### 3.5.4. በኢኮኖሚ ላይ

ኢንዱስትሪዎች የሚፈለገውን መስፈርት ሳያሟሉ ፍሳሾችን ወደ ውሃው አካል (ወንዝ እና ሀይቅ) ያፈሳሉ። እንደ ቁልፍ መረጃ ሰጪዎች ከሆነ እንስሳት ከተበከለው ውሃ ይጠጣሉ። በዚህ መልኩ የተበከለ ውሃ የሚጠጡ እንስሳት ለበሽታ አልፎ ተርፎም ለሞት ይጋለጣሉ። ይህም የገበሬውን ማህበረሰብ ኢኮኖሚ እየጎዳ ነዉ።

<u>**ኬዝ ሶስት**</u>

ሠንጠረዥ 1 እና 2 እና ምስል 4 ፋብሪካዎቹ ከሕብረተሰብ ጋር ያላቸዉን ቁርኝት የሚያሳዩ ናቸዉ። ሠንጠረዥ 1 እና 2 እና ምስል 4 ውስጥ ያሉትን ሃሳቦች መሰረት በማድረግ በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ ሃሳባችሁን ለሌሎች ተሳታፊዎች አጋሩ።

1. በሰንጠረዦቹና ምስሎቹ መሰረት የቆዳ ፋብሪካዎቹ በተቀመጡት መስፈርቶች መሰረት የተቋቋሙ ይመስላችኋል? መልስዎትን ያብራሩ።
2. የቆዳ ፋብሪካዎቹ እስካሁን ማሟላት የነበረባቸውን መስፈርቶች ለምን አላሟሉም?
3. በሰንጠረዦቹና ምስሎቹ የተመለከቱት ሁነቶች በአካባቢው ማህበረሰብ እና አካባቢ ላይ ምን ተጽዕኖ ይኖራቸዋል?
4. በሰንጠረዦቹና ምስሎቹ ሙስናን የሚያመላክቱ ጽንሰ-ሐሳቦች አሉ?
5. ለነዚህ ችግሮች መነሻ ምክኒያቶቸ ምን ሊሆኑ ይችላሉ?
6. እንዚህ ችግሮች እንዴት ሊፈቱ ይችላሉ?

| የቆሻሻ ማጣሪያ | ኢንዱስትሪዎች ብዛት | ማጣሪያ ያላቸዉ ኢንዱስትሪዎች | | ውጤታማ ይሆኑ ማጣሪያዎቸ | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | No | % | No | % |
| የመጀመሪያ | 21 | 21 | 100 | 15 | 71.42 |
| ሁለተኛ | 21 | 16 | 79.19 | 9 | 42.86 |
| ሶስትኛ | 21 | - | - | - | - |
| ክሮምን መልሶ መጠቀም | 21 | 4 | 19.05 | 4 | 19.05% |

ሠንጠረዥ 1፡ የቆዳ ፋብሪካዎች ያሉዋቸዉና ስራ እየስሩ ያሉ ቆሻሻ ማጣሪያ (FDEEPA፣ 2022)

| ተ.ቁ | ፊዚኮ-ኬሚካል መለኪያ በ(MG/L) | የብክለት ዉጤት በአማካይ | መለኪያ (MG/L) |
|---|---|---|---|
| 1 | Nitrate ($NO_3^-$) | 107 | 20 |
| 2 | Sulfide($S^{-2}$) | 7.3 | 1 |
| 3 | Chloride ($CL^-$) | 3279 | 1000 |
| 4 | Total Nitrogen (TN) | 960 | 60 |
| 5 | Chemical Oxygen Demand (COD) | 2167 | 500 |
| 6 | Ammonia (NH3) | 233 | 30 |
| 7 | Phenol | 8 | 1 |

ሠንጠረዥ 2፡ ከሰባት ከተመረጡ የቆዳ ፋብሪካዎች የተገኘ የተበከለ ውሃ ላብራቶሪ ምርመራ ውጤት (FDEEPA፣ 2022)





ምስል 5፡ በፋብሪካዎች የተበከለ ውሃ በእንስሳት ሲጠጣ (ፎቶው በፍቃዱ በልዳ ሚያዝያ 14 እና 8 ቀን 2022)

እነዚሀ ፋብሪካዎች የተወሰኑት ረጅም እድሜ ያላቸዉ ሲሆኑ ከሌሎቹ ቅርብ ጊዜ የተቋቋሙ ናቸዉ። በፋብሪካዎች ላይ በአካባቢው የሚኖር ተጎጂ ማህበረሰብ በየቀኑ ቅሬታ ያሰማል። እስካሁን ድረስ ምንም መፍትሄ አልተገኘም። ለቁጥጥር/ክትትል የሚሄዱት ግለሰቦችም መጀመሪያ የአካባቢውን ማህበረሰብ የመርዳት ስሜት ይዘው ሲመጡ ከቁጥጥር/ክትትል በኂላ ግን የተለየ ስሜት ይፈጥራሉ። የአካባቢውን ማህበረሰብ ችግር ከመቅረፍ ወደ መተቸት፤ መኮነንና ማሸማቀቅ ሲዞሩ ይስተዋላሉ።

### 3.6. የኢንዱስትሪ ዘርፍ የሙስና መከላከያ ስልቶች

የሚከተሉት ነጥቦቸ ሙሰናን ለመከላከል የሚያስችሉ ነጥቦች ናቸዉ።

### 3.6.1. የዘርፉን የሰው ሃይል ማጎልበት

ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን ለመከላከል የዘርፉን የሰው ሃይል **በእውቀት፣ በክህሎት እና በአመለካከት** መገንባት ዋነኛው የመከላከያ ስልት ነው፡፡ ሰራተኞች የተቋማቸውን ራእይና ተልእኮ እንዲሁም እሴት ጠንቀቀው ሊያውቁ ይገባል፡፡ ተቋማቸው የሚሰራባቸውን የህግ ማእቀፎች የስራ መመሪያዎችና ደንቦችን ማወቅ ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል በእጅጉ ይረዳል፡፡ በተለይ ሰራተኞች ስራቸውን ስነ-ምግባርን የተላበሰ አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ በሥነ-ምግባራር ጉዳይ ላይ አመለካከትን የሚቀርጹ የስነ-ምግባር ስልጠናዎችን በየጊዜው መስጠት ተገቢ ነው፡፡ ሙያዊ ብቃታቸውንም እንዲያጎለብቱ ሙያዊ ስነ-ምግባርን የሚያሻሽሉ ስልጠናዎች ሊዘጋጁ ይገባል፡፡

### 3.6.2. ግልጽነትና ተጠያቂነት ማስፈን

#### 3.6.2.1. ግልጽነት

የግልጽነት ጉዳይ ትክክለኛና ወቅታዊ መረጃን ለዜጎች የማድረስ ጉዳይ ነው፡፡ ዜጎች ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃ ማግኘት ከቻሉ አሰራሮች ሁሉ ግልጽ ስለሚሆኑ ለአስተዳደር በደል፣ ለብልሹ አሰራር ወይም ለሙስና ሰለባ አይሆኑም፡፡

ዘርፎች በሴክተሩ የሚሰጠውን መንግስታዊ አገልግሎት በተመለከተ ምን ዓይነት አገልግሎት፣ በምን መስፈርት፣ ለማን እንደሚሰጥ በዝርዝር የሚያብራራ መመሪያ ማውጣትና ተጠቃሚው ህብረተሰብ ይህንኑ በሚገባ እንዲያውቅ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

በመንግስት አሰራር ውስጥ የግልጽነት አሰራር ከሌለ ዜጎች የሚፈልገውን መረጃ በሚፈልገው ወቅትና መጠን ሊያገኝ አይችልም፡፡ ይህ ደግሞ መብቱን ለመጠየቅና ለማስከበር እንቅፋት ከመፍጠሩም ባሻገር ፈጻሚውን አካል ተጠያቂ ማድረግ አይችልም፡፡

### 3.6.2.2. ተጠያቂነት+

የተጠያቂነት አሰራር ማለት ስራውን የሚሰራው አካል ስራውን በአግባቡ መስራት እንዳለበት እና እንዲሰራ የተሰጠውን ኃላፊነት በአግባቡ ካልተወጣ፣ ለፈፀመው ጥፋት የሚጠየቅበት /በቅጣት ወይም ካሳ በመክፈል/ ስርአት ማለት ነው፡፡ ይህ እውን እንዲሆን ግን የሚጠይቅ ማለትም ስራህን በአግባቡ ሰርተሀል ወይም አልሰራህም በማለት ለመከታተል፣ ለመቆጣጠርና እንደሚፈለገው ሆኖ ሳይገኝ ሲቀር ኃላፊነትን መወጣት በውስጥ ያሉ አሰራሮች፣ ደንቦችና እሴቶችን ባግባቡ ተግባራዊ ማድረግ ሲሆን፣ ተጠያቂነት ደግሞ ለውጭ ጠያቂ አካል ምላሽ መስጠት ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡ ተጠያቂነት ተግባራዊ ከሚሆኑበት መንገዶች መካከል የተሰሩ ስራዎችን በተመለከተ፣ ለህግ አውጪው አካል፣ በየደረጃው ላሉ ሃላፊዎች ሪፖርት ማቅረብ፣ ለሚነሱ ጥያቄዎች ምላሽ መስጠት፤ ተጠያቂነት መንግስት የሚሰጠውን ስራ በአግባቡ በመስራት፣ ህብረተሰብን ለማገልገል ፈቃደኛ በመሆንም ይገለጻል፡፡

### 3.6.3. የሥነ-ምግባር ደንብን ተግባራዊ ማድረግ

በሙስና መከላከል ስትራቴጂ ውስጥ ሙስናን ለመከላከል ከሚጠቀሱ ዘዴዎች መካከል አንዱ የሥነ-ምግባር ደንብ አዘጋጅቶ ተግባራዊ ማድረግ ነው፡፡ በአንድ ተቋም ውስጥ የሥነ-ምግባር ደንብ መኖሩ በተቋሙ ውስጥ ተቀባይነት ያለው የሥነ-ምግባር ደረጃ እንዲሰፍን ይረዳል፡፡ የተቋሙ ሃብት በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውል፣ አድሎአዊነት እንዲወገድ፣ ቅንነትና ታማኝነት እንዲሰፍን ይረዳል፡፡ በተጨማሪም ግልጽነትና ተጠያቂነት እንዲኖር፣ የተሰጠን ሃላፊነትም ባግባቡ ለመወጣት የሥነ-ምግባር ደንብ አስፈላጊ መሳሪያ ነው፡፡ የሥነ-ምግባር ደንብ ማንኛውም ስራ ሲሰራ ሥነ-ምግባርን በተላበሰ መልኩ መሆን እንዳለበት ስለሚደነግግ ለሙስና እና ለብልሹ አሰራር የሚያጋልጡ የሥነ-ምግባር ባህርያትን ለመግታት ትልቅ አስተዋጽ አለው፡፡

የሥነ-ምግባር ደንቡን ተግባራዊ በማድረግ ረገድ ሁሉም ሰራተኛ ተሳታፊ የሚሆንበትን መንገድ መቀየስም ተገቢ ነው፡፡ በመጨረሻም ለሚከሰቱ የሥነ-ምግባር መተላለፎችን አግባብ ላለው አካል እንዲጠቁሙ ማድረግ፣ በመጠቆማቸውም ምክንያት መገለል እና ሌሎች ጥቃቶች እንዳይደርስባቸው መከላከል ይገባል፡፡

### 3.6.4. የሃብትና ጥቅም ማሳወቅና ማስመዝገብ

በየዘርፉ ሊከሰት የሚችለውን ሙስናና ብልሹ አሰራር ለመከላከልና ተጠያቂነትን ለማስፈን ከሚጠቅሙ የመከላከያ ስትራቴጂዎች መካከል በዘርፉ ውስጥ ያሉ ሰራተኞችና የስራ ሃላፊዎች ሃብታቸውን እንዲያሳውቁና እንዲያስመዘግቡ ማድረግ አንዱ ነው፡፡ የሃብት ማሳወቅና ምዝገባ ሕጋዊና ትክክለኛ የሥራ ፍሬ የሆነን ሃብት ምንጩ ካልታወቀ ሀብት ለመለየት ያስችላል፡፡ ከዚህ ባሻገር ውሳኔ ሰጪዎች ውሳኔ በሚሰጡበት ጊዜ በጥቅም ግጭት ሙስና ውስጥ እንዳይገቡ ያግዛል፡፡

የመወያያ ጥያቄ

- የሃብት ምዝገባ በምን መልኩ ምንጩ ያልታወቀ ሃብት መሰብሰብ ወንጀልን ለመከላከል ያስችላል?

### 3.6.5. የጥቅም ግጭትን የሚፈጥሩ ሁኔታዎችን መከላከል

የጥቅም ግጭት (CONFLICT OF INTEREST) ከመንግስት ወይም ከህዝብ የተሰጠውን ሃላፊነት ባግባቡ እንዲወጣ አደራ የተሰጠው የስራ ሃላፊ ወይም ባለስልጣን በስራ ተግባር እና ሃላፊነቱ ዉስጥ ከህዝብ፣ ከመንግስትና ከሃገር ጥቅም ይልቅ የግሉን፤ የቤተሰቡን ወይም የራሱን የቅርብ ዘመዱን የገንዘብ ወይም ማንኛውም ሌላ ጥቅም የማስቀደም ሁኔታ ሲያጋጥም ወይም ከመንግስታዊ ስራ ወይም ኃላፊነት ጋር በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ግጭት ሊፈጥር የሚችል ሁኔታ ነው፡፡

የጥቅም ግጭት ማንኛውም ዓይነት ኃላፊነትና ስልጣን ባለበት ሁኔታዎች እና አካባቢ ውስጥ እንደሚኖር ይታመናል፡፡ በመሆኑም በዘርፉ ውስጥ ያሉ የስራ ሃላፊዎችና ሰራተኞች ለዜጎች አገልግሎት በሚሰጡበት ወቅት ከሃላፊነታቸው ጋር በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ የጥቅም ግጭት ውስጥ ሊከታቸው የሚችሉ ሁኔታዎች ሲያጋጥማቸው ግጭቱን በመከላከል ወይም ባግባቡ ማስተዳደር የሚችሉበትን ስልት ሊቀይሱ ይገባል፡፡ ለምሳሌ በተቋማት ለጥቅም ግጭት ሊፈጥሩ የሚችሉ አሠራሮችንና አደረጃጀቶችን በጥናት መለየትና የጥቅም ግጭት እንዳይከሰት ለመከላከል የሚያስችል አሰራርን መዘርጋት፣ ሲፈጠርም አፋጣኝ እርምጃ መውሰድ ይገባል፡፡

### 3.6.6. የዘርፉን የፀረ-ሙስና ሚና ሚንስትሪም/የስራ አካል ማድረግ

የጸረ-ሙስና ትግል የአንድ ሰሞን ወይም የዘመቻ ስራ አይደለም፡፡ ዘርፎች ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ቁርጠኛ መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡ ቁርጠኝነታቸው ከሚገለጽባቸው መንገዶች መካከል  የጸረ-ሙስና ሚናን የስራቸው አካል ወይም ሜይንስትሪም ሊያደርጉ ይገባል፡፡ ይህም ሲባል ዘርፎች የጸረ-ሙስና ትግልን የእቅዳቸውና፣ የየእለት የስራ እንቅስቃሴያቸው፣ የሪፖርትና የውጤት ግምገማ አካላቸው ሊያደርጉት ይገባል ማለት ነው፡፡ የተቋሙ ማህበረሰብም በተደራጀና በተቀናጀ መልኩ የሚያደርጉትን የጸረ-ሙስና እንቅስቃሴ በባለቤትነት ስሜት ላይ በመመስረት ተሳትፏቸውን ከፍ ሊያደርጉ ይገባል፡፡  ከዚህ አንፃር እያንዳንዱ ተቋም ሙስናን ለመከላከልና ለመዋጋት የሚረዳው አደረጃጀት ፈጥሮ ወደ ትግሉ በቁርጠኝነት እንዲገባ ያግዘው ዘንድ የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎችን ማጠናከር ይጠበቅበታል፡፡

<u>አስረጂ</u>

- የኢንዱስትሪ ዘርፉን የፀረ-ሙስና ሚና እንደዘርፉ የስራ አካል አድረጎ አለማየት በዘርፉ የሚታይ አንዱ ችግር ነዉ፡፡

### 3.6.7. የመንግስት  የስራ ሃላፊዎች ሚናን  ማጠናከር

የተቋማት የስራ መሪዎች በተቋማት ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ግንባር ቀደም መሆናቸው ይታወቃል፡፡ ከዚህ አኳያ በየተቋሙ ያሉ የስራ ሃላፊዎች ራሳቸውን የመልካም ስነ-ምግባር አርዓያ ከማድረግ ጀምሮ ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል በርካታ ተግባራት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ከነዚህም መካከል፡-

- በተቋም ውስጥ ሥነ-ምግባራዊ አመራርን ተግባራዊ ማድረግ፣
- ሙስናን የመከላከል ስራን በተቋም ውስጥ ሜይንስትሪም ማድረግ፣
- ሥነ-ምግባራዊ ባህል በተቋም ውስጥ እንዲሰፍን ማድረግ፣
- የጥቅም ግጭትን የመከላከከያ ስትራቴጂዎችን ነድፎ ተግባራዊ ማድረግ፣
- የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድን እንዲወጣ እና ተግባራዊ እንዲደረግ ማድረግ፣

- በተቋሙ የአሰራር ስርዓት እንዲተገበር ለሙስና በር የሚከፍቱ አሰራሮችን ማሻሻል፣
- በስነ-ምግባራቸው የላቁና በአገልግሎታቸው የተመሰገኑ ሰራተኞችን እውቅና መስጠት፣

### 3.6.8. ከባለድርሻ አካላት ጋር በትብብርና በቅንጅት መስራት

በአንድ ዘርፍ ውስጥ ሥነ-ምግባርን ማስፈንና ሙስናን መከላከል ለዘርፉ ብቻ የሚተው እንቅስቀሴ ሳይሆን የባለድሻ አካላትንም ንቁ ተሳትፎ የሚጠይቅ ነው፡፡ ምክንያቱም ባለድርሻን ያላሳተፈ የፀረ-ሙስና እንቅስቃሴ ረጅም ርቀት መጓዝ አይችልምና ነው፡፡ ከዚህ አኳያ ህብረተሰቡ በዘርፉ የሚከሰቱ ሙስናና ኢ-ስነምግባራዊ ድርጊቶችን በማጋለጥ ሃላፊነታቸውን እንዲወጡ ማድረግ የሚችሉበትን ሁኔታዎች ማመቻቸት ይገባል፡፡ እንዲሁም ዘርፎች ግልጽነትና ተጠያቂነትን ለማስፈን በዚህ ዙሪያ ከሚሰሩ የሲቪል ማህበራትና የሙያ ማህበራት ጋር በቅንጅትና በትብብር ሊሰሩ ይገባል፡፡

<u>አስረጂ</u>

በኢንዱስትሪ ዘርፍ የስነምግባር ክፍሉ ከሌሎች የተቋሙ አደረጃጀቶች ጋር በቅንጅት የሚሰራበት መደበኛ አሰራር አለመኖሩ ዘርፉን ለሙስና ክሚያጋልጡ ሁነቶቸ እንደ አንዱ ተነስቷል፡፡

### 3.6.9. ቴክኖሎጂን ጥቅም ላይ ማዋል

በአገልግሎት አሰጣጥ ሂደት ተገልጋዮችን ለሙስና የሚያጋልጥ እንግልትን ለማስቀረት ቴክኖሎጂን ተግባራዊ ማድረግ ጠቃሚ ነው፡፡ ቴክኖሎጂ ለሙስና የሚያጋልጥ የተንዛዛ ቢሮክራሲን በማሳጠርና ቀልጣፋ አገልግሎት እውን እንዲሆን በማድረግና ተግባራት ከሰዎች ንክኪ ነጻ እንዲሆኑ በማድረግ ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ወቅቱ የሚጠይቀው የመከላከያ ስልት ነው፡፡ በመሆኑም በዘርፉ ያሉ ሰራተኞች ሙስናን መከላከል የሚያስችል የቴክኖሎጂ ፈጠራዎችን በመስራት፣ ራሳቸውን ለአዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ዝግጁ በማድረግ በቴክኖሎጂ ሙስናና ብልሹ አሰራርን የመከላከል ሃላፊነታቸውን ሊወጡ ይገባል፡፡

## 3.7. በኢንዱስትሪ ዘርፍ የሙስና ስጋቶች መከላከያ ስልቶች

### 3.7.1. ከኤክስፖርት ማበረታቻ እና ድጋፍ

- ሙያዊ ሥነ ምግባርን ጠብቀው እንዲሠሩ ግንዛቤ መፍጠር
- የቁጥጥር ሥርዓትን ማጠናከር
- የስራዎችን አፈጻጸም ወጥነት ባለው መልኩ መከታተልና መገምገም
- የተጠያቂነት ያለዉ የአሠራር ስርዓት መዘርጋት
- ተገልጋዮች በአገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ ለሚያነሱት ጥያቄ ፈጣን የማስተካከያ ምላሽ የሚሰጥበት ስርዓት መዘርጋት

### 3.7.2. <u>ከዉጪ ባለሙያዎችን የስራ ፍቃድ አሰጣጥ እና እድሳት</u>

- የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት ቀድሞ መከላከል
- ጠንካራ ክትትል እና ቁጥጥር ማድረግ
- በመጣበት ዉል መሠረት የተክኖሎጂ ሽግግር ያላደረጉ ድርጅቶች የስራ ፍቃዳቸዉን መሰረዝ የሚያስችል የህግ ስርዓት መዘርጋት\

### 3.7.3. የብቃትና ፈቃድ አገልግሎት አሰጣጥ

- ሙያዊ ሥነ ምግባርን ጠብቆ እንዲሠሩ ግንዛቤ መፍጠር
- የቁጥጥር ሥርዓትን ማጠናከር
- የተጠያቂነት አሠራርን ማስፈን
- የአሰራር ክፍተቶችን በመለየት አዳዲስ የአሰራር ስርዓት መዘርጋት

### 3.7.4. የማማከር፣ የጥናት እና ምርምር ስራ

- <u>ሙያዊ ሥነ ምግባርን ጠብቆ እንዲሠሩ ግንዛቤ መፍጠር</u>
- <u>የቁጥጥር ሥርዓትን ማጠናከር</u>

- <u>የተጠያቂነት አሠራርን ማስፈን</u>
- <u>የአሰራር ክፍተቶችን በመለየት አዳዲስ የአሰራር ስርዓት መዘርጋት</u>
- <u>የጥናትና ምርምር ዉጤታማነትን በጥብቅ ዲሲፕሊን መምራት</u>

### 3.7.5. መንግስት ለባለሀብቱ ከሚሰጣቸዉ የማበረታቻ እና ማስፋፍያ እንዲሁም ግብዓት ድጋፍ

- የተጠያቂነት ስርዓት መዘርጋት
- ጠንካራ እና ተከታታይነት ያለዉ ቁጥጥር ስርዓትን በማጠናከር ህጋዊ እርምጃ መዉሰድ
- ለባለሀብቶች ግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን መፍጠር
- ለስራዉ ተገቢ የሆኑ ህጎችና ደንቦችን ማሻሻል
- የተሰሩ የግብዓት ምርት ጥምርታ ጥናቶች መሠረት በማድረግ ምላሽ መስጠት

### 3.7.6. <u>ኢንተርፕራይዞችን መደገፍና ማልማት</u>

- የተጠያቂነት ስርዓት መዘርጋት
- ጠንካራ እና ተከታታይነት ያለዉ ቁጥጥር ስርዓትን በማጠናከር ህጋዊ እርምጃ መዉሰድ
- ለስራዉ ተገቢ የሆኑ ህጎችና ደንቦችን ማሻሻል
- የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን መፍጠር

### 3.7.7. የአላቂ እና ቋሚ እቃዎች እንዲሁም የአገልግሎት ግዥ

- <u>ንብረቶች በተጠየቀው ስፔስፊኬሽን መሰረት መገዛታቸውን በተጠናከረ መልኩ የመከታተያ ስርዓት መዘርጋት</u>
- <u>የአሰራር መመሪያዎች በትክክል ተግባራዊ መደረጋቸውን መቆጣጠር</u>
- <u>ግልፅና ተጠያቂነት ያለው አሰራር ማጠናከር</u>
- <u>አቅም ገንቢ የሆኑ ስልጠናዎችን ማመቻቸት</u>
- <u>የጨረታ ኮሚቴ፣ የቴክኒክ ኮሚቴዎች እና የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ ህግና ስርዓት ጠብቀዉ እንዲሰሩ ክትትል ማድረግ</u>

### 3.7.8. <u>መሠረታዊ አገልግሎት እና ንብረት አስተዳደር</u>

- የተጠያቂነት ስርዓትን ማጠናከር
- የቁጥጥርና የክትትል ስርዓትን ማጠናከር
- ንብረቶች በተዘጋጀው ስፔስፊኬሽን መሰረት እንዲገቡ የተዘረጋውን ስርዓት በትክክል መተግበር
- የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎችን ማካሄድ
- የዳሰሳ ጥናት በማካሄድና ችግሮችን በመለየት የተገልጋይን እርካታ ማሳደግ
- ደንብና መመሪያዎችን በአግባቡ ተግባር ላይ ማዋል

### 3.7.9. የብቃትና የሰው ሀብት አስተዳደር

- ህግና መመሪያን ተከትሎ መስራት
- ግልፅና ተጠያቂነት ያለበት አሰራር መዘርጋት
- የመረጃዎችን ትክክለኛነት ማረጋገጥና ከተለያዩ ተቋማት ጋር ግንኙነት መፍጠር
- አሰራሮችን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፉ ማድረግ

## 3.8. የማጠቃለያ ጥያቄዎች

ኢንዱስትሪ በተለያዩ መንገዶች የሚያደርሰውን ጉዳትና የመከላከያ ስልቶ አስመልክቶ ስልጠና ከወሰዳችሁ በኋላ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን ተወያይታችሁ መልሱ፡፡

1. በህብረተሰባችን ላይ የሚደርሱ የተለያዩ ችግሮች በኢንዱስትሪና ተጠሪ ተቋማት በሚከሰቱ ሙስና ምክኒያት ስለመሆናቸዉ የምታዉቁትን አብራሩ፡፡
2. በዚህ ሞጁል ንዑስ ክፍል ዉስጥ ከተመለከቱት ዉጭ በኢንዱስትሪ ዘርፍ ያለዉ ሙስና የሚያደርሰውን ጉዳት አብራሩ፡፡
3. ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች በቡድን ተወያይታችሁ የደረሳችሁበትን ለተሳታፊዎች አቅርቡ፡

4. በዚህ ስልጠና ከተመለከታችኋቸው የመከላከያ ስልቶች መካከል በዘርፋችሁ ተግባራዊ የተደረጉት የትኖቹ ናቸው? የተገኘውስ ለውጥ ምን ይመስላል?
5. በዚህ ስልጠና ውስጥ ከተመለከታችሁት የሙስና መከላከያ ስትራቴጂ መካከል በዘርፋችሁ ተግባራዊ ያልተደረጉት የትኖቹ ናቸው? ምክንያቱስ ምንደነዉ?
6. ከምትሰሩበት የስራ አካባቢ አንጻር ቴክኖሎጂን በመጠቀም ሙስናና ብልሹ አሰራርን እንዴት መቀነስ እንደሚቻል በዝርዝር ለተሳታፊዎች አስረዱ፡፡
7. በዚህ ስልጠና ካያችኋቸው በተጨማሪ ሙስናና ብልሹ አሰራርን መከላከል የሚያስችሉ ስትራቴጂዎች ካሉ ለተሳታፊዎች አስረዱ፡፡

## 3.9. ማጠቃለያ

በኢንዱስትሪ ዘርፍ የሚከሰት ሙስና በተቋማቱ፣ በሕብረተሰብ፣ በአከባቢና በሰላምና ደህንነት ከፊተኛ ተፅኖዎችን እያስከተለ ይገኛል፡፡ ሙስና ሃብትን ከአምራች ወደ አባካኝ እንዱስትሪዎች በማዞር የኢኮኖሚ ዕድገትን ያዳክማል፤ የተዛባ የገበያ ውድድር፡ ያስከትላል፡፡ ውጤታማ ያልሆኑ እንዱስትሪዎች ኮንትራቶችን እንዲያሸንፉ በማድረግ በሕብረተሰብ፣ በአከባቢና በሰላምና ደህንነት ችግር እነዲከሰት ያደርጋል፡፡ ሙስና ብቃትን መሰረት ያደረጉ ውሳኔዎችን በመሸርሸር በአሰራር ላይ ብቃት ማነስን በማበረታታትና የኢንዱስትሪውን ተወዳዳሪነት በአገር ውስጥ እና በአለም አቀፍ ደረጃ ይቀንሳል፡፡የውጭ ባለሀብቶች በሙስና በሚጠረጠሩ ኢኮኖሚዎች ላይ ኢንቨስት ለማድረግ ሊያቅማሙ ይችላሉ፣ ይህም የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት እንዲቀንስ ያደርጋል፡፡ በሸቀጦች እና አገልግሎቶች ላይ የዋጋ ንረትን ያስከትላል፡፡ ይህም ለተጠቃሚዎች እና ለመንግስት ከፍተኛ ወጪን ያስከትላል፡፡ የሙስና ጥቅማጥቅሞች ወደ ጥቂት ስግብግብ ግለሰቦች በመሄድ የገቢ አለመመጣጠን እያባባሰ የብዙሃኑ ድህነት እንዲባባስ ያደርጋል፡፡

ህዝቡ በመንግስት እና በንግድ ተቋማት ላይ ያለውን እምነት በመሸርሸር ማህበራዊ አለመረጋጋት እና በባለስልጣናት ላይ እምነት ማጣት አስከትሏል፡፡

በኢንዱስትሪዎች የሚስተዋለው ሙስና እንደ ጤና አጠባበቅ፣ ትምህርት እና መሠረተ ልማት ባሉ ጥራት ያለዉ አገልግሎት እንዳይኖር በማድረግ በታችኛዉ እርከን ያሉ የማህበረሰብ ክፍሎችን ይጎዳል፡፡

በፈሳሽና በደረቅ መልኩ በኢንዱስትሪ ዘርፍ የሚለቀቁ በካዮች በቤት አንስሳቶች ተጠጥተዉና ተበልተዉ ሆዳቸዉ ዉስጥ ትላትል በመፍጠር በአግባቡ እንዳይመገቡ በማድረግ፤ ጉበትና የምግብ መፍጫ አካላትን በመጉዳት፤ ፀጉር በማርገፍ፤ ተቅማጥ በማስከተል፤ በመቀብተት፤ በማሳል፤ በመጨረሻ ሞትን ያስከትላሉ። ይህ በሕብረተሰቡ ላይ የትየለሌ ጉዳቶችን ያደርሳል።

መከላከል ማለት አንድ ሁኔታ ወይም ችግር ከመፈጠሩ በፊት ወይም ተፈጥሮም ከሆነ ሰፋ ያለ ጉዳት ከማድረሱ በፊት አስፈላጊ እርምጃዎችን በመውሰድ ችግሩ በመፈጠሩ ይደርስ የነበረውን ጉዳት ሙሉ በሙሉ እንዳይፈጠር ማድረግ ወይም የጉዳቱን መጠን ዝቅተኛ እንዲሆን ማድረግ ነው። ሙስናና ብልሹ አሰራርን የመከላከል ተግባርም በአንድ ዘርፍ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች ሊያስከትሉ የሚችሉትን ከፍተኛ የሆነ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ኪሳራ ለማስቀረት ወይም ለመቀነስ በሚያስችል መልኩ የችግሩን ምንጭ የማድረቅ ተግባር ነው። በአንድ ዘርፍ ውስጥ ሊከሰቱ የሚችሉ የሙስናና የብልሹ አሰራርን መከላከል የሚያስችል ብቸኛና ወጥ የሆነ የመከላከያ ሥልት የለም። ይሁንና እንደተቋሙ ባህሪና ተልዕኮ እንዲሁም በየጊዜው የሚለዋወጠውን የሙስና ስትራቴጂ ግምት ውስጥ ያስገባ የሙስና መከላከያ ስትራቴጂ ነድፎ ተግባራዊ ማድረግ ይገባል። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የሙስና እና ብልሹ አሰራርን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ ዘጠኝ ስትራቴጂዎች ተመላክተዋል። ይሁንና የመከላከያ ስልቶቹ ስምንት ብቻ ናቸው ማለት እንዳልሆነ ሰልጣኞች ልብ ሊሉ ይገባል። ልምዳቸውንና እውቀታቸውን በመጠቀም ልዩ ልዩ የሙስና መከላከያ ስትራቴጂዎችን በማምጣት የበኩላቸውን ሃላፊነት ሊወጡ ይገባል።

## 4. ዋቢ

ADDIS STANDARD **(GETAHUN LEGESSE).** DECEMBER 12, 2022**.** WILL ETHIOPIA'S LATEST CRACKDOWN ON CORRUPTION REVERSE THE "RED CARPET" INTO "RED LINE"? ADDIS STANDARD. **ADDIS ABABA.**

ALTENBURG, T. (2010). *INDUSTRIAL POLICY IN ETHIOPIA: DISCUSSION PAPER.* GERMAN DEVELOPMENT INSTITUTE, 1(45).

FIKADU BELDA, IMANA, G., LEMESSA, A., & DODA, Z. (2024). LAND ACQUISITION FOR INDUSTRIAL DEVELOPMENT AND ITS REPERCUSSIONS ON THE PEACE OF THE LOCAL FARMING COMMUNITIES IN LUME DISTRICT, OROMIA, ETHIOPIA. *COGENT SOCIAL SCIENCES*, *10*(1). HTTPS://DOI.ORG/10.1080/23311886.2024.2306031

MOHAMMED ALI. (2002). INDUSTRIAL POLLUTION AND ITS IMPACT ON THE LITTLE AKAKI RIVER, MSC THESIS, FACULTY OF ENGINEERING, LOUGHBOROUGH UNIVERSITY, UK.

NDIAYA, C. AND LV, K.J. (2018). ROLE OF INDUSTRIALIZATION ON ECONOMIC GROWTH: THE EXPERIENCE OF SENEGAL (1960-2017). *AMERICAN JOURNAL OF INDUSTRIAL AND BUSINESS MANAGEMENT*, 8: 2072-2085.

ኢንዱስቲሪ ሚኒስቴር. (2016). የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር እና ተጠሪ ተቋማት የሙስና መከላከያ ስትራቴጂክ እቅድ (ከ2017 እስከ 2023 ዓ.ም). አዲስ አበባ፡ ኢትዮጵያ.

የፌደራል የስነ ምግባርና ጸረ ሙስና ኮሚሽን. (2015 ዓ/ም). የሙስና ወንጀልች በጠቅላላው የማሰልጠኛ ሞጁል). አዲስ አበባ፡ ኢትዮጵያ.

የፌደራል የስነ ምግባርና ጸረ ሙስና ኮሚሽን. (2015 ዓ/ም). የኢንዱስትሪ ዘርፍ የሙስና *ሥጋት* ግምገማዊ ጥናት፡፡ አዲስ አበባ፡ ኢትዮጵያ.

## አባሪ አንድ፦ ራስን መገምገሚያ ቼክ ሊስት

### ቅድመ ስልጠና ቼክ ሊስት

"በኢንዱስትሪ ዘርፍ ሙስና መከላከል" በሚል ርዕስ በሰንጠረዡ ውስጥ በተቀመጡት የስልጠና ፍሬ ጉዳዮች ላይ ያላችሁን ግንዛቤና እና እውቀት በተቀመጡት ሃሳቦች ትይዩ (√) ምልክት በማድረግ ይግለጹ፡፡

| ተ.ቁ | ሃሳቦች | ዝቅተኛ | ጥሩ | በ. ጥሩ |
|---|---|---|---|---|
| 1. | ስለ ሙስና ፍቺና ማብራሪያ | | | |
| 2. | ስለ ሙሰና አሰክፊነት | | | |
| 3. | የሙስና ምንነት | | | |
| 4. | የሙስና ዓይነቶች | | | |
| 5. | የሙስና ወንጀል ምንነት | | | |
| 6. | በአዋጅ ቁጥር 881/2007 የተደነገጉ የሙስና ወንጀሎች | | | |
| 7. | ሙስናና ብልሹ አሠራር | | | |
| 8. | የሙስና ተግባር ውስብስብነት በኢንዱስትሪ ዘርፍ | | | |
| 9. | የሙስና ምንጮች በኢንዱስትሪ ዘርፍ | | | |
| 10. | በኢንዱስትሪ ዘርፍ የሙስና መንሳኤዎች | | | |
| 11. | የሙስና ማሳያ ምልክቶች | | | |
| 12. | ሙስና በአገርና በህዝብ ላይ የሚያደርሰው ጉዳት | | | |
| 13. | ሙስናን ከማህበረሰብ እውቀትና ግንዛቤ ጋር በሚስማማ መንገድ መግለጽ እንደሚቻል፡፡ | | | |
| 14. | ሙስናን ከማህበረሰብ እውቀትና ግንዛቤ ጋር በሚስማማ መንገድ በመግለጽ የበለጠ ማስረጽ እንደሚቻል፡፡ | | | |
| 15. | ሙስናን መከላከል ለተቋማዊ አፈፃፀም ያለው ፋይዳ | | | |
| 16. | ሙስናን በአገሪቱ ሁለንተናዊ እድገት ላይ የሚኖረው አሉታው ተፅዕኖ | | | |
| 17. | በዘርፉ የሚስተዋለውን ሙስናና ብልሹ አሠራርን ለመከላከል የሚደረገው ጥረት አስፈላጊ ስለመሆኑ | | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 18. | የኢንዱስትሪ ዘርፉ የሙስና ተጋላጭነት | | | |
| 19. | ኢንዱስትሪ ዘርፍን ለሙስና የሚያጋልጡ ሁኔታዎች | | | |
| 20. | የተቋማት አመራሮች ለምን የሥነ ምግባርና የጸረ ሙስና ክፍልን በበጎ እንደማይመለከቱ | | | |
| 21. | የሚጠበቅባችዉን መስፈርቶች ሳያሟሉ የተቋቋሙ ኢንዱስትሪዎች እንዳሉ | | | |
| 22. | በሙስና የተነሳ ኢንዱስትሪዎች የሚያደርሱት ኢኮኖሚያዊ፣አከባቢያዊ እና ማህበረሰባዊ ቀዉሶች ስለመኖሩ | | | |
| 23. | የተለያዩ ችግሮች በኢንዱስትሪ ዘርፉ በሚከሰቱ ሙስናዎች በማህበረሰባችን ላይ የሚደርሱ መሆናቸውን | | | |
| 24. | ሙስናን ለመከላከል የሚረዱ የሙስና መከላከል ስልቶች | | | |
| 25. | ከሙስና መከላከል ስልቶች የበለጠ ውጤታማ የሆኑትን | | | |
| 26. | ሙስና አትራፊ እንዳልሆነ | | | |
| 27. | ሙስና አዋራጅ/አቅላይ እንደሆነ | | | |

**የድህረ ስልጠና ቼክ ሊስት**

"በኢንዱስትሪ ዘርፍ ሙስና መከላከል" በሚል ርዕስ በሰንጠረዥ ውስጥ በተቀመጡት የስልጠና ፍሬ ጉዳዮች ላይ በስልጠናው ያገኛችሁትን ግንዛቤና እውቀት በመስፈርቶቹ ትይዩ (√) ምልክት በማድረግ ግለጹ።

| ተ.ቁ | ሃሳቦች | ዝቅተኛ | ጥሩ | በ. ጥሩ |
|---|---|---|---|---|
| 1. | ስለ ሙስና ፍቺና ማብራሪያ | | | |
| 2. | ስለ ሙሰና አስከፊነት | | | |
| 3. | የሙስና ምንነት | | | |
| 4. | የሙስና ዓይነቶች | | | |
| 5. | የሙስና ወንጀል ምንነት | | | |
| 6. | በአዋጅ ቁጥር 881/2007 የተደነገጉ የሙስና ወንጀሎች | | | |
| 7. | ሙስናና ብልሹ አሠራር | | | |
| 8. | የሙስና ተግባር ውስብስብነት በኢንዱስትሪ ዘርፍ | | | |
| 9. | የሙስና ምንጮች በኢንዱስትሪ ዘርፍ | | | |
| 10. | በኢንዱስትሪ ዘርፍ የሙስና መንሳኤዎች | | | |
| 11. | የሙስና ማሳያ ምልክቶች | | | |
| 12. | ሙስና በአገርና በህዝብ ላይ የሚያደርሰው ጉዳት | | | |
| 13. | ሙስናን ከማህበረሰብ እውቀትና ግንዛቤ ጋር በሚስማማ መንገድ መግለጽ እንደሚቻል። | | | |
| 14. | ሙስናን ከማህበረሰብ እውቀትና ግንዛቤ ጋር በሚስማማ መንገድ በመግለጽ የበለጠ ማስረጽ እንደሚቻል። | | | |
| 15. | ሙስናን መከላከል ለተቋማዊ አፈፃፀም ያለው ፋይዳ | | | |
| 16. | ሙስናን በአገሪቱ ሁለንተናዊ እድገት ላይ የሚኖረው አሉታው ተፅዕኖ | | | |
| 17. | በዘርፉ የሚስተዋለውን ሙስናና ብልሹ አሠራርን ለመከላከል | | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | የሚደረገው ጥረት አስፈላጊ ስለመሆኑ | | | |
| 18. | የኢንዱስትሪ ዘርፉ የሙስና ተጋላጭነት | | | |
| 19. | ኢንዱስትሪ ዘርፍን ለሙስና የሚያጋልጡ ሁኔታዎች | | | |
| 20. | የተቋማት አመራሮች ለምን የሥነ ምግባርና የጸረ ሙስና ክፍልን በበጎ እንደማይመለከቱ | | | |
| 21. | የሚጠበቅባቸዉን መስፈርቶች ሳያሟሉ የተቋቋሙ ኢንዱስትሪዎች እንዳሉ | | | |
| 22. | በሙስና የተነሳ ኢንዱስትሪዎች የሚያደርሱት ኢኮኖሚያዊ፣ አከባቢያዊ እና ማህበረሰባዊ ቀዉሶች ስለመኖሩ | | | |
| 23. | የተለያዩ ችግሮች በኢንዱስትሪ ዘርፉ በሚከሰቱ ሙስናዎች በማህበረሰባችን ላይ የሚደርሱ መሆናቸውን | | | |
| 24. | ሙስናን ለመከላከል የሚረዱ የሙስና መከላከል ስልቶች | | | |
| 25. | ከሙሰና መከላከል ስልቶች የበለጠ ውጤታማ የሆኑትን | | | |
| 26. | ሙስና አትራፊ እንዳልሆነ | | | |
| 27. | ሙስና አዋራጅ/አቅላይ እንደሆነ | | | |

## አባሪ ሁለት፦ በሰፊ ቡድን ለማወያያ የሚሆኑ ጥያቄዎች

1. በኢንዱስትሪ ዘርፉ ተዘዉትረው የሚታዩት የሙስና ወንጀል ዓይነቶች የትኞቹ ናቸው? ለምን?
2. ከኢንዱስትሪ ዘርፉ ለሙስና መንስዔ የሆኑና ሊሆኑ የሚችሉ ሁነቶች ምንድናቸዉ?
3. በኢንዱስትሪ ዘርፍ ዉስጥ ስለመከሰቱ የሚታዉቁትን አንድ የሙስና ድርጊት ከግማሽ ነጭ ወረቀት ባላነስ ከሙሉ ነጭ ወረቀት ባልበለጠ መጠን ጽፋችሁ ለአሰልጣኙ አስረክቡ። አሰልጣኞች ከነዚህ መሀል ጠቃሚ ናችዉ ብለዉ ያሰቡትን በመምረጥ ለመማማሪያነት ያቅርቡ።
4. በኢንዱስትሪ ዘርፍ የሚፈጸሙ ሙስናዎች አገርን እንዴት ሊጎዱ እንደሚችሉ አብራሩ።
5. በኢንዱስትሪ ዘርፍ የምታውቋቸውን የሙስና እና የብልሹ አሰራሮች መከላከያ ስልቶችና ጥቅማቸውን ዘርዝሩ።

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን
FEDERAL ETHICS AND ANTI-CORRUPTION COMMISSION

ስልክ;- +251115-52-77-85/+251115-53-69-01
ፖሳቁ P.O.Box :- 34798/99
ኢ-ሜይል:- E-mail FeaccEthiopia2013@et
ፌስቡክ/www.facebook.com/feaccOfficial
ድረ-ገጽ/ www.feacc.gov.et